# የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

?? ? ??? ? ? ? ?? ?? ?? ??? ? ??

?? ? ?? ?? ? ? ? ? ? ?? ?? ? ? ? ? ???? ??? ?? ?

??? ? ?? ??? ? ? ? ? ?? ??? ??? ?? ????

???? ?? ? ?? ??

???? 2016 ?.?

??? ???

**ማውጫ**


***የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶች*** (Executive Summery)....................................................i

***ክፍል አንድ*** ............................................................................................................1

***መግቢያ*** ..................................................................................................................1

የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ዓላማ፤ ሥልጣንና ተግባር..........................................2

የኮርፖሬሽኑ አላማዎች .....................................................................................................2

የኮርፖሬሽኑ ራዕይ ....................................................................................................2

የኮርፖሬሽኑ ተልዕኮ ....................................................................................................3

የኮርፖሬሽኑ ስልጣንና ተግባር .......................................................................................3

የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር................................................................................................3

የኮርፖሬሽኑ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል......................................................................4

የኮርፖሬሽኑ የሰው ሃይል......................................................................................................5

የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ ምንጭ.................................................................................................6

የኮርፖሬሽኑ የዜናና ወቅታዊ ዘርፍ የፋይናንስ አፈፃፀም ...................................................................7

የኦዲቱ አላማ ...................................................................................................................8

የክዋኔ ኦዲቱ የኦዲት አካባቢ.....................................................................................................8

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች .....................................................................................................8

የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች .....................................................................................................8

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ..............................................................................................................9

የሬዲዮና የቴሌቪዥን የዜናና ወቅታዊ ጉዳዮች አገልግሎት የአሰራር ስርዓት መግለጫ/Process Description/.....10

***ክፍል ሁለት*** ..........................................................................................................12

***ግኝቶች*** ...................................................................................................................12

I. የኮርፖሬሽኑ የስራ አመራር ቦርድ ኮርፖሬሽኑን በብቃት ለመምራት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፤ ..........................................................................12

የስራ አመራር ቦርዱ የራሱ የሆነ የአሰራር መመሪያ ማውጣቱን በተመለከተ ..........................................12

የስራ አመራር ቦርዱ የመገናኛ ብዙሃንን በሚመለከት የወጡ የመንግስት ፖሊሲዎች እና ህጎች በኮርፖሬሽኑ ተግባራዊ መደረጋቸውን ማረጋገጡን በተመለከተ .......................................................................13

የስራ አመራር ቦርዱ በኮርፖሬሽኑ የሚቀርቡ ፕሮግራሞች የሃሳብና የይዘት ብዝሃነት ያላቸው መሆናቸውን መከታተሉን በተመለከተ..........................................................................................................14

የስራ አመራር ቦርዱ ኮርፖሬሽኑ በሚሰጠው አገልግሎት ህዝቡ ተጠቃሚ መሆኑን የሚገመግምበት የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ ........ 15

የስራ አመራር ቦርዱ ኮርፖሬሽኑ ሚዛናዊ የሆነ የራዴዮና የቴሌቪዥን አገልግሎት መስጠቱን መከታተሉን በተመለከተ ........ 16

የስራ አመራር ቦርዱ የፕሮግራም ይዘት የሚገመግምበትና ስለሚሻሻልበት ሁኔታ ሃሳብ ማቅረቡን በተመለከተ .. 17

የስራ አመራር ቦርዱ ከአድማጭ ተመልካቾች ቅሬታዎችን የሚመረምር እና ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን በተመለከተ ........ 18

የስራ አመራር ቦርዱ የኮርፖሬሽኑን የሚያቀርባቸው ፕሮግራሞች ተደራሽ መሆናቸውን መከታተሉን በተመለከተ 19

የኮርፖሬሽኑ የስራ አመራር ቦርድ አመራር የስብሰባ ጊዜን በተመለከተ ........ 20

II. ኮርፖሬሽኑ የሬዲዮና የቴሌቪዥን የዜና አገልግሎትን በብቃት ለመስጠት የሚያስችል መመሪያ፣ ስታንዳርድ እና የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ ........ 21

ኮርፖሬሽኑ የኦዶቪዥዋል አርካይቭ ዲጂታላይዝ ማደረጉን በተመለከተ ........ 21

ኮርፖሬሽኑ የኤዲቶሪያል ፖሊሲውን መከለሱን በተመለከተ ........ 22

III. ኮርፖሬሽኑ የሬዲዮና ቴሌቪዥን የዜና አገልገሎት ሽፋንን፤ ተደራሽነትንና ስብጥርን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመስጠት የሚያስችለው የአሰራር ሥርአት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን መገምገምን በተመለከተ ........ 23

ኮርፖሬሽኑ ኤዲቶሪያል ነፃነት በተጠበቀ ከማንኛውም አካል ነፃና ገለልተኛ መሆኑን በተመለከተ ........ 23

ኮርፖሬሽኑ በቋንቋዎች የሚያሰራጫቸው ስርጭቶች ሽፋንን በተመለከተ ........ 25

ኮርፖሬሽኑ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ወይም ድርጅቶችን በፍትሃዊነት የሚያገለገልበት የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ ........ 26

ኮርፖሬሽኑ የሰብአዊ መብቶች መከበራቸውን አጉልቶ የሚያሳይ የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ ........ 28

ኮርፖሬሽኑ ተቃራኒ ሃሳቦች የሚስተናገዱበት የክርክር ፕሮግራም የሚያዘጋጅ መሆኑን በተመለከተ ........ 31

ኮርፖሬሽኑ በሚያስተላልፋቸው የዜና ዘገባዎች የስርጭት ጥራታቸውና ተደራሽነት በተመለከተ ........ 33

ኮርፖሬሽኑ የዜና ዘገባ የሁነትና የፕሮጀክት በሚያሳይ መልኩ መሆኑን በተመለከተ ........ 35

IV. የኮርፖሬሽኑን የዜና አገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል የሚችሉ የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፤ ........ 37

ኮርፖሬሽኑ በሚያቀርባቸው ዘገባዎች እና ፕሮግራሞች ላይ የዳሰሳ ጥናት ማከናወኑን በተመለከተ ........ 37

ኮርፖሬሽኑ የአድማጭ ተመልካችን ቅሬታዎችን መፍታቱን በተመለከተ ........ 38

***ክፍል ሶስት*** ........ 40

***መደምደሚያ*** ........ 40

***ክፍል አራት*** ........ 42

***ማሻሻያ ሀሳቦች*** ........ 42

**አባሪ 1፡- በኦዲት ሥራ የተከለሱ ሰነዶች ዝርዝር** ..... i

አባሪ 2፡- የመመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) ..... ii

አባሪ 3፡- በኢትዮጵያ ሬዲዮ እና በኤፍ ኤም 97.1 ከአድማጭ ተመልካች ግበረ መልስ ሪፖርት ውስጥ ከማህበረሰቡ ከቀረቡ ቅሬታዎች ውስጥ ለማሳያ ያህል ..... vi

አበሪ 4 ፡- **በኮርፖሬሽኑ በ2015 ዓ.ም የተሰሩት የዜና ስብጥሮች የሚያሳይ** ..... vii

አባሪ 5፡- የራዲዮ የስርጭት ጥራትና ተደራሽነትን ችግር ያለባቸው አካባቢዎች የሚያሳይ መረጃዎች ..... viii

**አባሪ 6፡- ኢዜማ ካወጣቸው መግለጫዎች በኮርፖሬሽኑ የዘገባ ሽፋን የሰጣቸውና ያልሰጣቸው መግለጫዎች የሚያሳይ** ..... xiv

**አባሪ 7 ፡-የኮርፖሬሽኑ ድርጅታዊ መዋቅር** ..... xvi

የዜናና ወቅታዊ ዘርፍ መዋቅር ..... i

**አበሪ 8፡- የአሰራር ስርዓት መግለጫ** (System Description) ..... xvii

**አባሪ 9 ፡-የሬዲዮ ትራንስሚተሮች የማስተላለፍ አቅማቸውን የሚያሳይ ሰንጠረዥ** ..... xxi

**የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶች** (Executive Summery)

በ21ኛው ክፍለ ዘመን የሚዲያ ሥራ እጅግ ውስብስብና ሰፊ እየሆነ፣ ተፅዕኖውም እየጠነከረ መጥቷል፡፡ ሚዲያ በሚያሰራጫቸው መረጃዎች አማካይነት አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የሀገር ግንባታን ለመደገፍ በድምጽና በምስል መረጃ ስርጭት ትውልዱን የመቅረጽና የማነጽ ተልዕኮ ያለው የመንግስትና የህዝብ ተቋም ነው፡፡ ተቋሙ በኢትዮጵያ የበኩር ድምጽ የሆነ እና ረጅም ታሪክ ያለው በመሆኑም በብዙ የድልና የሀሴት እንዲሁም የችግርና የፈተና ወቅቶች ከኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊያን ጋር አብሮ የቆየና የተቆራኘ ተቋም ነው፡፡

የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በአለም አቀፍ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (International Standards For Supreme Audit Institutions -ISSAI) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 ዓ.ም በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ነው፡፡ ኦዲቱ የተከናወነው በኮርፖሬሽኑ የሬዲዮና የቴሌቪዥን የዜናና ወቅታዊ ጉዳዮች አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ሲሆን ኦዲቱ የሸፈነውም ጊዜ ከ2013 ዓ.ም እስከ ጥር 2015 ዓ.ም ድረስ ያለውን በጀት ዓመት አፈፃፀምን ሲሆን፤ ይህንኑ በተመለከተ መረጃዎችን ከኮርፖሬሽኑ እና ከባለድርሻ አካላት ቃለመጠይቅ በማድረግ፣ ማስረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በመተንተን እና ሌሎች የኦዲት ዘዴዎችን በመከተል የክዋኔ ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የሚሰራቸው የሬዲዮና የቴሌቪዥን የዜናና ወቅታዊ ጉዳዮች አገልግሎት አሰጣጥ አፈፀፃም ብቃት ያለውና ውጤታማ መሆኑን መገምገም ሲሆን በዚህ ዙሪያ የሚታዩ የአሰራር ክፍተቶች ካሉ በመለየት ችግሮቹን ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

ከላይ የተጠቀሰውን የክዋኔ ኦዲት ዓላማ ለማሳካት አራት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ ተለይተዋል፡፡እነሱም፡-

1. የስራ አመራር ቦርዱ ኮርፖሬሽኑን በብቃት ለመምራት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፤
2. የኮርፖሬሽኑ ሬዲዮና ቴሌቪዥን የዜና አገልግሎት ለመስጠት መመሪያ፣ ስታንዳርድ እና የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም ፤
3. የኮርፖሬሽኑን የሬዲዮና የቴሌቪዥን የዜና አገልገሎት ሽፋን፤ ተደራሽነትንና ስብጥር ውጤታማ የአሰራር ሥርአት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም እና

4. የኮርፖሬሽኑን የዜና አገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል የሚችሉ የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣ የሚሉ ናቸው፡፡

በዚህ መሠረት በኦዲቱ ወቅት የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የኮርፖሬሽኑ የስራ አመራር ቦርዱ የራሱ የስራ መመሪያ እንደሚያወጣ በኮርፖሬሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ ቢገለፅም ከዚህ አንፃር የተዘጋጀ መመሪያ የሌለ መሆኑ፣
- የኮርፖሬሽኑ ስራ አመራር ቦርድ የመገናኛ ብዙሃንን በሚመለከት የመንግስት ፖሊሲዎችን እና ህጎችን በኮርፖሬሽኑ ተግባራዊ መሆናቸውን የሚያረጋግጥበት የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣
- የኮርፖሬሽኑ ስራ አመራር ቦርድ በኮርፖሬሽኑ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ሚዲያዎች የሃሳብና የይዘት ብዝሃነት ያላቸው ፕሮግራሞች ተቀርፀው ለህዝብ መቅረባቸውን የሚከታተልበት የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣
- የኮርፖሬሽኑ ስራ አመራር ቦርድ ኮርፖሬሽኑ በሚሰጠው አገልግሎት ህዝቡ ተጠቃሚ መሆኑን የሚገመግምበት የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣
- የኮርፖሬሽኑ ስራ አመራር ቦርድ የተለያዩ አመለካከት ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶችና የህብረተሰብ ክፍሎች ሚዛናዊ የሆነ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ፍትሃዊ አገልግሎት ማግኘታቸውን የሚከታተልበት የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣
- የኮርፖሬሽኑ ስራ አመራር ቦርድ በራዲዮ፣ በቴሌቪዥን ፣ በዲጅታል ሚዲያ እና በሌሎች ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች የሚተላለፈውን የፕሮግራም ይዘት የሚገመግምበትና ስለሚሻሻልበት ሁኔታ ሃሳብ የሚያቀርብበት የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣
- የኮርፖሬሽኑ ስራ አመራር ቦርድ ከአድማጭ ተመልካቾች በኮርፖሬሽኑ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የሚመረምርበትና ተገቢውን ውሳኔ የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣
- የኮርፖሬሽኑ ስራ አመራር ቦርድ የኮርፖሬሽኑን ፕሮግራሞች በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ተደራሽ መሆናቸውን የሚከታተልበት የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ
- የኮርፖሬሽኑ ቦርድ አመራር ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ስብሰባውን የማያደርግ መሆኑ፣ እንዲሁም ቦርዱ ኮርፖሬሽኑን ወደ ተሻለ ምዕራፍ ሊያሸጋግሩ የሚችሉ

እቅዶችን አቅዶ ከመስራት አንፃርና የተቋሙን ጊዜያዊና ዘላቂ ችግሮችን ለመቅረፍ በሚያስችል መልኩ ወቅቱን የጠበቀ ግንኙነት በማድረግ ረገድ ክፍተት ያለበት መሆኑ፤

- ኮርፖሬሽኑ የአርካይቭ ሀብትን ዲጅታላዝ ለማድረግ በተለይም የድሮ ካሴቶች መገልበጫ ማሽን በሀገር ውስጥ አለመኖር ሲሆን ኮርፖሬሽኑ ይህንን ማሽን በግዢ ወይም በኪራይ ለማግኘት እንዲቻል በጀት እንዲፈቀድ ለገንዘብ ሚኒስቴርና ለፕላን ሚኒስቴር ጥያቄ የቀረበ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ችግሩ ያልተፈታ መሆኑ፤

- ኮርፖሬሽኑ የሚዲያውን ኢንዱስትሪ እና የአገሪቱን የእድገት ሽግግር ከግምት ውስጥ በማስገባት የኤዲቶሪያል ፖሊሲው ወቅታዊ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ኮርፖሬሽኑ ኤዲቶሪያል ነፃነት በተጠበቀ እና በሥራውም ሆነ በአስተዳደሩ መንግሥትና የመንግሥት ተቋማትን ጨምሮ ከማንኛውም አካል ነፃና ገለልተኛ ሆኖ እየሰራ አለመሆኑ፤
- ኮርፖሬሽኑ ከይዘት አንፃር የሚሰራቸው ስራዎች ከመንግስት በሚሰጠው አቅጣጫ ተከተሎ እንደሚሰራና በመንግስት ጫና የሚደርስበት መሆኑና እንዲሁም ሚዲያው በነፃነት እየሰራ አለመሆኑ፤
- ኮርፖሬሽኑ በሚያቀርባቸው ዜናዎችም ሆነ ፕሮግራሞች የሰብአዊ መብቶች መከበራቸውን አጉልቶ የሚያሳይ የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፤ እንዲሁም የተለያዩ ሰብዓዊ መብት ድርጅቶች የሚያወጧቸው መግለጫዎችን በብዛት የዘገባ ሽፋን የማይሰጥ መሆኑ፤
- ኮርፖሬሽኑ ተቃራኒ ሃሳቦች የሚስተናገዱበትና ሃሳባቸውን የሚገልፁበት የክርክር ፕሮግራም እና ውይይት መድረኮችን በ2015 ዓ.ም ማዘጋጀት የጀመረ ቢሆንም በቂ አለመሆኑ፤
- ኮርፖሬሽኑ የሬዲዮ ስርጭትን በተመለከተ በ2013 ዓ.ም ባስጠናው ጥናት መሰረት አብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች የኢትዮጲያ ሬዲዮ ስርጭት የማይሰማ መሆኑ መገለፁ፤
- ኮርፖሬሽኑ ካሉት 43 የሬዲዮ ማሰራጫ ጣቢያዎች እና የኤፍ ኤም ትራንስሚተሮች የተወሰኑት የሬዲዮ ማሰራጫ ጣቢያዎች እና የኤፍ ኤም ትራንስሚተሮች የሚያሰራጩት ካላቸው አቅም በታች መሆኑ፤

- ኮርፖሬሽኑ የሬዲዮ ስርጭት ጥራት ችግርና ተደራሽነት ላይ በተደጋጋሚ ከህዝብ ቅሬታዎች የሚነሱ ቢሆንም በኮርፖሬሽኑ በኩል ችግሮቹን እንዲፈቱ ያላደረገ መሆኑ፤
- የኮርፖሬሽኑ ኤፍ ኤም ማሰራጫ ጣቢያዎች በብዛት ከተማ አካባቢ የተተከሉ በመሆኑ ተደራሽነታቸው ለከተማ አካባቢ ላሉ ማህበረሰቦች ብቻ በመሆኑ በገጠሩ አካባቢ ለሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች በኤፍ ኤም የሚተላለፉ የኢትዮጵያ ሬዲዮ ስርጭቶች ተደራሽ አለመሆናቸው፤
- ኮርፖሬሽኑ የመካከለኛ ሞገድ ሬዴዮ ማሰራጫ ጣቢያዎች ለረዥም አመታት ያገለገለ፣ ከቴክኖልጂ እድገት አንጻር ኋላ ቀርና፣ የመለዋወጫ ዕቃ እጥረት ያለባቸውና የስርጭት ጥራት ደረጃቸውም ዝቅተኛ መሆናቸው፤
- የመብራት መቋረጥን ተከትሎ ስርጭቱን በጀነሬተር ለመሸፈን ቢሞከርም ጀነሬተሮቹ ረዘም ላለ አመታት ያገለገሉ በመሆናቸው በአሁኑ ሰዓት ከፍተኛ የነዳጅ ፍጆታ ስለሚጠቀሙ ጥዋትና ማታ ለአንድ ስዓት ብቻ እንዲሰሩ የሚደረግበት ሁኔታ መኖሩ፤
- ኮርፖሬሽኑ ከሚሰራቸው የዜና ዘገባዎች አብዛኛው የሁነት ዘገባ መሆኑንና የፕሮጀክት ዜናዎች ላይ ትኩረት አደርጎ እየሰራ አለመሆኑ፤
- ኮርፖሬሽኑ በሚያቀርባቸው ዘገባዎች እና ፕሮግራሞች ላይ የህዝቡን ስሜት ለማወቅ በናሙና ላይ የተመሰረተ ተከታታይነት ያለው የዳሰሳ ጥናት በራስ አቅምም ሆነ በገለልተኛና ሙያዊ ብቃት ባላቸው የውጭ አካላት ያላስጠና መሆኑ፤
- ኮርፖሬሽኑ የአድማጭ ተመልካች ቅሬታዎችን ግብረመልስ የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፤ እንዲሁም ኮርፖሬሽኑ ለአድማጭ ተመልካቾች በምን ሁኔታ እና መቼ ግብረ መልስ መስጠት እንዳለበት በግልፅ የተቀመጠ የአሰራር ስርዓት የሌለው መሆኑ፤ የሚሉት ናቸው፡፡

**ከላይ የተገለፁት ግኝቶች ለመቅረፍ ይችላሉ ተብለው የታመነባቸውን የማሻሻያ ሀሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡**

- የኮርፖሬሽኑ የስራ አመራር ቦርዱ የራሱ የስራ የሆነ መመሪያ ሊያወጣ እና ኮርፖሬሽኑ የሚሰራቸውን ስራዎችን ሊከታተል፣ ሊቆጣጠር እና የማሻሻያ ሃሳብ ሊያቀርብ ይገባል፡፡

- የሥራ አመራር ቦርዱ ኮርፖሬሽኑን ወደ ተሻለ ምዕራፍ ሊያሸጋግሩ የሚችሉ እቅዶችን አቅዶ በመስራት የተቋሙን ጊዜያዊና ዘላቂ ችግሮችን ለመቅረፍ በሚያስችል መልኩ ወቅቱን የጠበቀ ግንኙነት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ የአርካይቭ ሀብትን ዲጅታላዝ በማድረግ ለመያዝ ከፍተኛ ችግር የሆነው በተለይም የድሮ ካሴቶች መገልበጫ ማሽን በሀገር ውስጥ አለመኖር መሆኑን የገለፁ ሲሆን፤ ይህንን ማሽን በግዢ ወይም በኪራይ ለማግኘት እንዲቻል ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት እንደ ለገንዘብ ሚኒስቴርና ለፕላን ሚኒስቴር ትኩረት በመስጠት ዲጂታላይዝ በማድረግ የሀገር ሀብት ከትውልድ ትውልድ እንዲተላለፍ፤ ለምርምርና ለትምህርት እንዲውል ሊያደርጉ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ የኤዲቶሪያል ፖሊሲውን ተጨባጭ ሁኔታዎችንና ወቅቱ የሚጠይቀውን የሚዲያ ኢንዱስትሪውን ለውጥና ዕድገት በማካተት በየአምስት አመቱ ሊከልስ ይገባል፡፡ እንዲሁም የኤዲቶሪያል ፖሊሲው ተከትሎ በሚወጡ መመሪያዎች ላይ በየጊዜው ክፍተታቸውን እየፈተሹ ደረጃቸውን እንዲጠብቁም ሆነ የአሰራር ውጤታማነት እንዲያስገኙ ሊያድግ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ በአገሪቱ ሕገ መንግሥትና የምርጫ ሕግ መሠረት የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ወይም ድርጅቶችን በፍትሃዊነት የሚያገለግልበት እና የሰብአዊ መብቶች መከበራቸውን አጉልቶ የሚያሳይ ስራዎችን መስራት ይኖርበታል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ የሬድዮ ስርጭት በቀላሉ ከቦታ ቦታ ይዞ በመንቀሳቀስ ወቅታዊ መረጃ ከዳር እስከ ዳር በማዳረስ፣ በማስተማር፣ በማዝናናት እንዲሁም መንግስትንና ህዝብን እንደ ድልድይ ሆኖ በማገናኘት አውንታዊ ሚና የሚጫወት በመሆኑ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራ ይገባል::
- ኮርፖሬሽኑ የአድማጮች የእርካታ ደረጃ በምን ያህል ደረጃ እንደሆነ ፣ ተቀባይነቱ እና ፍላጐት እንዲቀጥሉ እና አዲስ እንዲተከሉ የሚፈልጓቸው ወይም የማይፈልጓቸው ፕሮግራሞች ለመለየትና የኮርፖሬሽኑን ቴሌቪዥንንና ሬድዮንን እንዳይከታተሉ የሚያደርጋቸው ዋና ዋና ምክንያቶች እና የስርጭት ጥራቱና ያለበት ደረጃ ምን እንደሚመስልና ያሉትን ክፍተቶች ለመሙላት እና ለማሻሻል የሚያግዝ የዳሰሳ ጥናት ሊያካሂድ ይገባል፡፡

- ኮርፖሬሽኑ የአድማጭ ተመልካች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ግብረመልስ የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ኮርፖሬሽኑ ለአድማጭ ተመልካቾች በምን ሁኔታ እና መቼ ግብረ መልስ መስጠት እንዳለበት በግልፅ የተቀመጠ የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል ፡፡

# ክፍል አንድ
# መግቢያ

1. በዚህ ዘመን የሚዲያ ሥራ እጅግ ውስብስብና ሰፊ እየሆነ ተፅዕኖውም እየጠነከረ መጥቷል፡፡ ሚዲያ በሚያሰራጫቸው መረጃዎች አማካይነት አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡
2. የቴሌቪዥን አገልግሎት ሥራ ምንነትና ጠቀሜታው ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲታወቅ ያደረገው የብሪታንያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን (BBC) የተሰኘው የታላቋ ብሪታንያ ኩባንያ በ1948 ዓ.ም የንጉሠ ነገስት ኃይለ ሥላሴ የብር ኢዮቤል በዓል በሚከበርበት ጊዜ ነበር፡፡ የቢ.ቢ.ሲ ቴሌቪዥን ኩባንያ በቴሌ ኮሙኒኬሽን ውስጥ ሁለት ካሜራዎችን፣ አራት ሞኒተሮችንና ተጓዳኝ መሳሪያዎች በመጠቀም የቴሌቪዥንን ፕሮግራም ምንነት ለሕብረተሰቡ ያስተዋወቀው፡፡ በ1956 ዓ.ም ደግሞ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የሀገር ውስጥ መደበኛ ስርጭቱን ጀመረ፡፡
3. የኢትዮጵያ ሬዲዮ እና የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ራሳቸውን ችለው ለየብቻቸው አገልግሎት ሲሰጡ ቆይተው የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን በ1979 ዓ.ም አንድ ላይ የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት /ኤሬቴድ/ በመባል ተዋሃደ፡፡
4. የኢትዮጵያ የሚዲያ ኢንዱስትሪ በ1983 ዓ.ም የመጣውን የስርዓት ለውጥ ተከትሎ በአደራጃጀቱም ሆነ በይዘቱ መሰረታዊ ለውጥ በማስመዝገብ ላይ ይገኛል፡፡ በተለያዩ ስርዓቶች በመንግስት ባለቤትነት ተገድቦ በሳንሱር ተሸብቦ ለስርዓቶች የስልጣን መስበኪያ የዜጎች መጨቆኛ መሳሪያ ሁኖ ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጂ በ1985 ዓ.ም የፕረስ አዋጅ በፈጠረው ምቹ ሁኔታ መንግስት ብቸኛ የሚዲያ ባለቤት የሆነበትን አሰራር በማስወገድ የኢትየጵያ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ሀሳባቸውን በነፃ የሚያንሸራሽሩበት መድረክ ለመሆን ለማስቻል በተጨማሪም የግል ሚዲያዎችም ድርሻቸውን የሚያበረክቱበት እድል ተፈጥሯል፡፡
5. እንዲሁም ኮርፖሬሽኑ የገቢ አቅሙ የተጠናከረ ሁኖ ተልእኮውን በተሻለ ሁኔታ ለመወጣት በሀገሪቱ ሁለንታናዊ እድገትና ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሂደት የሚጠበቅበትን አዎንታዊ ሚና መወጣት እንዲችል ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑና የኮርፖሬሽኑ ስልጣንና ተግባር የተለያዩ ሁለት አዋጆች መመንጨቱ የአሰራር ክፍተት በመፍጠሩ በአንድ  አዋጅ ስር ማጠቃለል ተገቢ በመሆኑ እንዲሁም የኮርፖሬሽኑ ስራ አመራር ቦርድ ተቋሙን በተሻለ ሁኔታ የሚደግፍበትን ስርኣት ማስቀመጥ አስፈላጊ

በመሆኑ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1278/2015 ተብሎ እንደገና እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

6. በአሁኑ ወቅት በሀገራችን የተጀመረውን ፈጣን የሚዲያ ዘርፍ ዕድገትና መስፋፋት ላይ እንደመሆኑ የሚዲያ ዘርፍ ልማት ፍጹም አስፈላጊ የሆነ የፖለቲካዊ ፤የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መረጃዎች ለህዝቡ እየደረሱ አለመሆኑ የተለያዩ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚህ አንጻር ኦዲቱ መከናወኑ ለኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ከወዲሁ ችግሮቹን በመቅረፍ ውጤታማ እንዲሆን ስለሚረዳው የክዋኔ ኦዲቱ ለኮርፖሬሽኑ ጠቃሚ ነው፡፡

## የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ዓላማ፤ ሥልጣንና ተግባር

### የኮርፖሬሽኑ አላማዎች

7. ኮርፖሬሽኑ በአዋጅ ቁጥር 1278 /2015 መሰረት የሚከተሉት አላማዎች አሉት፡፡ እነርሱም፡-
   - በመገናኛ ብዙሃንና በሌሎች አግባብ ባላቸው ሕጎችና ፖሊሲዎች መሠረት በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ስለሚፈጸሙ አበይትና ወቅታዊ ጉዳዮች እንዲሁም ትምህርታዊና አዝናኝ ዝግጅቶችን በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥንና በድረ-ገጽ በማቅረብ፣ ከሕዝቡም በግብረ-መልስ ሥርዓት ወይም በቀጥታ የሚገኘውን ግብዓት በመጠቀም ሕዝቡ በሀገሪቱ በሚካሄደው ሁለተንናዊ ጉዳዮች ላይ ግንዛቤ ኖሮት በሀገር ልማት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን ማድረግ፤
   - በህዝቦች መካከል በመተማመን ላይ የተመሰረተ አንድነት እንዲጠነክር ትስስራቸው ስር እንዲሰድ እንዲሁም ብሔራዊ መግባባት በመፍጠር ወንድማማችነትና ህብረ ብሔራዊ አንድነትን ለማጎልበት የሚደረገውን ሀገራዊ ጥረት ማገዝ
   - ሀገሪቱ ጠንካራ የዲሞክራሲ ስርአት እውን እንዲሆን በሚደረገው ጥረት ውስጥ ቁልፍ ሚና መጫወት የሚሉት ናቸው፡፡

### የኮርፖሬሽኑ ራዕይ

8. በይዘቱና በአቀራረቡ የሕዝብ አመኔታን ያተረፈ ቀዳሚ የመረጃ ምንጭ የሆነ እና በአለም አቀፍ ደረጃ ተመራጭ የሚዲያ ተቋም በ2017 ዓ.ም ተፈጥሮ ማየት፡፡

## የኮርፖሬሽኑ ተልዕኮ

9. ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ አስተሳሳብ የበላይነት እንዲያገኝ፤ ሃገራዊ ገጽታ እና አህጉራዊ አንድነት እንዲጠናከር የኤዲቶሪያል መርህን በተከተለ አሳዋቂ፣ አስተማሪና አዝናኝ ይዘቶችን ዘመናዊ ቴክኖሎጂና የሰው ኃይል በመጠቀም አገልግሎት መስጠት::

## የኮርፖሬሽኑ ስልጣንና ተግባር

10.ኮርፖሬሽኑ በአዋጅ ቁጥር 1278 /2015 ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባራት መካከል፡-

- ሕዝብ ጠቃሚና አስፈላጊ የሆኑ ዜናዎችና መዋዕለ-ዜናዎችን ማሰባሰብ፣ ማዘጋጀትና በሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና በድረ-ገጽ በልዩ ልዩ የሀገር ውስጥና የውጭ ቋንቋዎች በማሠራጨት ለተገልጋዩ የማድረስ፤
- ለዲሞክራሲያዊ ስርኣት ግንባታ እና ለሀገራዊ አንድነት ህብረተሰቡን የሚያነሳሱ ለሁለንታናዊ እድገት፤ በህዝቦች መካከል መቀራረብን የሚያጎሉ እንዲሁም በመተማመን ላይ የተመሰረተ አንድነትን የሚያስችሉ ትምህርታዊና አሳዋቂ ፕሮግራሞችን የማቅረብና የመንግስት ህጎችና ፖሊሲዎችን ለህዝብ ማስተዋወቅ
- ሕዝቡ ስለሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ያለው ግንዛቤ እንዲዳብር የሚረዱ ፕሮግራሞችን የማቅረብ፣
- ነፃ የህዝብ አስተያየቶችንና ጥቆማዎችን ተቀብሎ የማስተላለፍ፤
- የሕዝቡን ዕውቀትና ፈጠራ የሚያዳብሩና የመዝናናት ፍላጎቱን የሚያረኩ ልዩ ልዩ ፕሮግራሞችን የማቅረብ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው ፡፡

## የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

11.የኮርፖሬሽኑ ስራዎች በበላይነት የሚመራና የሚቆጣጠር የስራ አመራር ቦርድ ያለው ሲሆን፤ኮርፖሬሽኑን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 1278 /2015 መሰረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ተሰጥቶታል፡-

- መገናኛ ብዙሃንን በሚመለከቱ የመንግስት ፖሊሲዎች እና ህጎች በኮርፖሬሽኑ ተግባራዊ መሆናቸውን የማረጋገጥ
- በህዝብ መታወቅ ያለባቸው የመንግስት ፖሊሲዎች እና ህጎች በወቅቱ መተላለፋቸውን ማረጋገጥ፣
- በኮርፖሬሽኑ የሚሰራጩ ፕሮግራሞች ሀገራዊ አንድነትና ብልፅግና ማረጋገጥ ላይ ግብ ያደረጉ መሆናቸውን መከታተል፣

- በኮርፖሬሽኑ የራዲዮ እና የቴሌቪዥን ሚዲየሞች የሃሳብና የይዘት ብዝሃነት ያላቸው ፕሮግራሞች ተቀርፀው ለህዝብ መቅረባቸውን መከታተል፣
- ኮርፖሬሽኑ በሚሰጠው አገልግሎት ህዝቡ ተጠቃሚ መሆኑን የመገምገም፤ህዝቡ በሚዲያው ይበልጥ ተጠቃሚ ስለሚሆንበት ሁኔታ ሃሳብ የማቅረብ፣
- የተለያየ አመለካከት ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የህብረተሰብ ክፍሎች ሚዛናዊ የሆነ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ፍትሃዊ አገልግሎት ማግኘታቸውን የማረጋገጥ፣
- በሬዲዮ፤ በቴሌቪዥን እና በዲጅታል ሚዲያ እና በሌሎች በኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች የሚተላለፈውን ፕሮግራም ይዘት የመገምገም እና ስለሚሻሻልበት ሁኔታ ሃሳብ የማቅረብ፣
- ከአድማጭና ተመልካች በኮርፖሬሽኑ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የመመርመር ፤ተገቢውን ውሳኔ የመስጠት፣
- በዚህ አዋጅና በኮርፖሬሽኑ ሰራተኞች አስተዳደር ደንብ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ቦርዱ መመሪያ ሊያወጣ በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ መመሪያ የማውጣት፡ የኮርፖሬሽኑ ሰራተኞች የደመወዝ፣ የአበልና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች ላይ የመወሰን፣
- ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመበትን አላማ ለማሳካት እንዲችል የዘመነ ቴክኖሎጂ ባለቤት የሚሆንበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤ የኮርፖሬሽኑ ፕሮግራሞች በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ተደራሽ መሆናቸውን መከታተል፤ እንዲሁም ኮርፖሬሽኑ የሚጠናከርበትንና አሰራሩ የሚሻሻልበትን ሁኔታ የመቀየስ፣
- የኮርፖሬሽኑን አመታዊ የስራ እቅድና የስራ እንቅስቃሴ ሪፖርት መገምገምና ማፅደቅ እንዲሁም በዋና ኦዲተር መ/ቤት የተላኩ የኦዲት ግኝቶች አፋጣኝ ምላሽ እንዲያገኙ ይከታተላል፣
- የኮርፖሬሽኑን አመታዊ የገቢና ወጪ በጀት ማፅደቅ፣
- ኮርፖሬሽኑን የሚመለከቱ ሌሎች የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ የመምከር፣የመወሰን የሚሉት ናቸው፡፡

## የኮርፖሬሽኑ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል

12.የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ተጠሪነቱ ለህዝብ ተወካዮች ም/ ቤት ሆኖ በቦርድ የሚመራ ሲሆን፣ በስሩ አንድ ዋና ስራ አስፈፃሚ ሲኖረው በዋና አስፈፃሚ ስር 1 ምክትል ዋና አስፈፃሚ እና ለዋና ስራ አስፈፃሚ ተጠሪ የሆኑ አምስት (5) ዘርፎችና

ስድስት(6) ዲፓርትመንቶች አሉት፡፡ ለምክትል ዋና አስፈፃሚ ስር ተጠሪ የሆኑ ደግሞ አራት (4) ዘርፎች ይገኛሉ፡፡ **ዝርዝሩም በአባሪ 7 ተያይዟል፡፡**

## የኮርፖሬሽኑ የሰው ሃይል

13.የሰው ሀይሉን በተመለከተ ለኮርፖሬሽኑ በመዋቅር በጠቅላላው 3873 የሰው ኃይል የተፈቀደ ሲሆን፣ እስከ ታህሳስ 2016 ዓ.ም በስራ ላይ ያለው የሰው ኃይል 2064 ማለትም 53.3 በመቶ መሆኑን ከሰው ሀብት አስተዳደርና ልማት ዲቪዥን ከተሰበሰበ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ የሰው ኃይል ስብጥሩ በፃታና የትምህርት ደረጃ ከታች ባለው ሰንጠረዥ ተገልፆል፡፡

| ተ.ቁ | በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ሃይል | በሥራ ላይ ያለ የሰው ሃይል | | | | በፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የትምህርት ደረጃ | ወንድ | ሴት | ድምር | |
| | | ፕሮፌሰር | 1 | - | 1 | |
| | | ዶክትሬት | 2 | 1 | 3 | |
| | | ማስተርስ | 137 | 53 | 190 | |
| | | ድግሪ | 607 | 277 | 884 | |
| | | ዲፕሎማ | 218 | 102 | 320 | |
| | | ዲፕሎማ በታች | 490 | 148 | 638 | |
| | | የትምህርት ደረጃ ያልተሞላ | 18 | 10 | 28 | |
| | 3873 | | 1473 | 591 | 2064 | 53.3% |

የዜናና ወቅታዊ ዘርፍ የሰው ኃይል ስብጥሩ በፃታና የትምህርት ደረጃ ከታች ባለው ሰንጠረዥ ተገልፆል

| ተ.ቁ | በመዋቅር የተፈቀደው | የትምህርት ደረጃ | በትምህርት | | | በፐርሰ ንት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ወን ድ | ሴ ት | ድም ር | |
| 1 | | ማስተር | 40 | 17 | 57 | |
| 2 | | ድግሪ | 148 | 52 | 200 | |
| 3 | | ዲፕሎማ | 14 | 4 | 18 | |
| 4 | | ከዲፕሎማ በታች | 4 | 4 | 8 | |
| 5 | | ትምህርት ያልተሞላ | 2 | 2 | 4 | |
| | 758 | ጠቅላላ ድምር | 206 | 78 | 284 | 37.8% |

## የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ ምንጭ

14.የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስፈልገውን ገቢ የሚያገኘው በመንግስት በሚደረግለት የድጋፍ በጀትና ኮርፖሬሽኑ ከሚያመንጨው የገቢ ምንጭ ነው ፡፡ ዝርዝሩ በሰንጠረዡ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| **የበጀት ዓመት** | **የበጀት ዓይነት** | **የተፈቀደ በጀት** | **ሥራ ላይ የዋለ በጀት** | **በስራ ላይ የዋለ በጀት በፐርሰንት** |
|---|---|---|---|---|
| 2013 | ከመንግስት ድጋፍ | 496,570,000.00 | 510,386,700.16 | 102.78% |
| | ከኮርፖሬሽኑ ገቢ | 500,745,559.74 | 141,096,534.88 | 28% |
| | ድምር | 997,315,559.74 | 651,482,235.04 | 65% |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 2014 | ከመንግስት ድጋፍ | 700,000,000.00 | 622,134,486.41 | 88.8% |
| | ከኮርፖሬሽኑ ገቢ | 579,587,086.73 | 327,150,192.34 | 56.4% |
| | ድምር | 1,279,587,086.73 | 949,284,678.75 | 74% |
| 2015 | ከመንግስት ድጋፍ | 990,000,000.00 | 1,007,622,891.07 | 101.7% |
| | ከኮርፖሬሽኑ ገቢ | 1,157,620,000.00 | 916,676,117.80 | 79.2% |
| | ድምር | 2,147,620,000.00 | 1,924,299,008.87 | 89.6% |
| **ጠቅላላ ድምር** | | 4,424,522,646.47 | 3,525,065,921 | 79.7% |

## የኮርፖሬሽኑ የዜናና ወቅታዊ ዘርፍ የፋይናንስ አፈፃፀም

| **የበጀት ዓመት** | **የተፈቀደ በጀት** | **ሥራ ላይ የዋለ በጀት** | **በስራ ላይ የዋለ በጀት በፐርሰንት** |
|---|---|---|---|
| 2013 | 33,181,000.00 | 11,122,833.15 | 33.5% |
| 2014 | 47,769,000.00 | 25,423,361.05 | 53.2% |
| 2015 | 81,103,350.00 | 68,330,677.42 | 84.2% |
| **ጠቅላላ ድምር** | 161,053,350.00 | 109,453,023.00 | 67.9% |

### ማስገንዘቢያ

የ2013 ዓ.ም የመንግስት ድጋፍ በጀት አፈፃጸሙ የበለጠበት ምክኒያት በ2012 ዓ.ም በተሰብሳቢ ተይዞ በ2013ዓ.ም ላይ በመወራረዱ እንዲሁም 2015 ዓ.ም የመንግስት ድጋፍ በጀት አፈፃጸሙ የበለጠበት ምክኒያት በ2014 ዓ.ም በጀት አመቱ በተሰብሳቢ ተይዘ የነበረ በ2015 ዓ.ም የተወራረደ በመሆኑ ነው፡፡

## የኦዲቱ አላማ

15.የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የሚሰራቸው የሬዲዮና የቴሌቪዥን የዜናና ወቅታዊ ጉዳዮች አገልግሎት አሰጣጥ አፈፀፃም ብቃት ያለውና ውጤታማ መሆኑን መገምገም የሚል ሲሆን፣ በዚህ ዙሪያ የሚታዩ የአሰራር ክፍተቶች ካሉ በመለየት ችግሮቹን ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳብ ለማቅረብና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

## የክዋኔ ኦዲቱ የኦዲት አካባቢ

16. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የሬዲዮና የቴሌቪዥን የዜናና ወቅታዊ ጉዳዮች አገልግሎት አሰጣጥ አፈፀፃም ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን መገምገም የሚል ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች

17.ከላይ በተለየው የኦዲት አካባቢ ሥር አራት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ ተለይተዋል፡፡ እነሱም

1. የኮርፖሬሽኑ የስራ አመራር ቦርድ ኮርፖሬሽኑን በብቃት ለመምራት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣
2. ኮርፖሬሽኑ ሬዲዮና ቴሌቪዥን የዜና አገልግሎትን በብቃት ለመስጠት የሚያስችል መመሪያ፣ ስታንዳርድ እና የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም፣
3. ኮርፖሬሽኑ የሬዲዮና የቴሌቪዥን የዜና አገልግሎት ሽፋን፣ ተደራሽነትንና ስብጥር ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመስጠት የሚያስችለው የአሰራር ሥርአት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም፣
4. ኮርፖሬሽኑ የዜና አግልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል የሚችሉ የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣ የሚሉት ናቸው፡፡

## የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች

18.ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠውን የኦዲት አካባቢ ለመገምገም የተለዩትን የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችን መሰረት በማድረግ 28 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የተዘጋጁት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶችም (Evaluative

Criteria) ለኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ተልከው አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹም ከዚህ ሪፖርት ጋር (በአባሪ 2) ተያይዟል፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

19. የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ላይ የክዋኔ ኦዲትን ለማካሄድ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ሥልጣን እና በአለም አቀፍ የዋና ኦዲተር መ/ቤቶች የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (International Standards of Supreme Audit Institutions (ISSAI) መሠረት ነው፡፡ ኦዲቱ የተከናወነው በኮርፖሬሽኑ የሬዲዮና የቴሌቪዥን  የዜናና ወቅታዊ ጉዳዮች  አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ሲሆን የሸፈነውም ጊዜ ከ2013 ዓ.ም እስከ ጥር 2015 ዓ.ም ድረስ ያለውን በጀት ዓመት አፈፃፀም ነው፡፡

20. ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን እና የኮርፖሬሽኑ ስራዎች በበላይነት የሚመራውና የሚቆጣጠረው የስራ አመራር ቦርድ ላይ ሲሆን፣ ከኮርፖሬሽኑ ውስጥ ካሉት የስራ ዘርፎች እና ክፍሎች በተጨማሪ ከኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ፤ከኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ  ፤ከኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ ፓርቲ ፤ከእናት ፓርቲ ፤ከኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ፓርቲ  ፤ከነፃነትና እኩልነት ፓርቲ  እና ከመላው ኢትዮጵያ  አንድነት ድርጅት ማስረጃዎችን በመከለስ፣ የሚመለከታቸውን የስራ ኃላፊዎች ቃለ መጠይቅ በማድረግ፣ መረጃዎችን በመተንተን የኦዲት ማስረጃዎች ተሰብስበዋል።

## የሬዲዮና የቴሌቪዥን የዜናና ወቅታዊ ጉዳዮች አገልግሎት የአሰራር ስርዓት መግለጫ/Process Description/

21.በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካትና አለም አቀፍ ተወዳዳሪ የሆነ የሚዲያ ተቋም እንዲሆን ይረዳኛል ያለውን የአሰራር ሥርዓት ዘርግቷል፡፡ ኮርፖሬሽኑ የዜናና ወቅታዊ ይዘቶችን ለማምረት ሁለት ዋና ዋና መንገዶች አደራጅቶ ይጠቀማል፡፡

- ➢ የሁነት ይዘት ፕሮዳክሽን፡- በውጭ አካላት ፍላጎት ሁነትን ተመርኩዞ የሚመጣን የሚዲያ ሽፋን የሚፈቀድበት አሰራር ነው
- ➢ የፕሮጀክት ዜና ፕሮዳክሽን ፡- ተቋሙ አገራዊና ነባራዊ ሁኔታ እንዲሁም የተቋቋመበትን ዓላማ መሰረት በማድረግ በአጀንዳነት ቀርፆ የሚሰራበት አካሄድ ነው

- ❖ እነዚህን ይዘቶች ወደ ፕሮዳክሽን ለመቀየር የሚያስፈልጉ እንደ ካሜራ፣ መኪና፣ፋይናንስ ተጨማሪ ሙያተኛ እና እና መሰል የሀብት ግባዓቶች ለማግኘት ተቋሙ በአንድ ማዕከል ዜናና ወቅታዊ ስራዎች የሚያስተዳድር የመረጃ ቋት (assignment desk) የተሰኘ ክፍል አለው::
- ❖ በመሆኑም ይዘቶች ከተቋሙ ኤዲቶሪያል ፖሊሲ እና አገራዊ ፍላጎት አንፃር የተቃኙና የተስማሙ መሆናቸው ታይቶ በኤዲቶሪያል ኮንፈረስ ክርክር ከተደርገበት በኃላ ፀድቆ ወደ ስራ ይገባል፣ ይህንን አሳይመንት ዴስኩ ተከታትሎ በማዕከላዊነት ለሁሉም ቻናሎች ቋንቋዎች ተደራሽ ሆኖ አገልግሎት ይሰጣል፡፡
- ❖ በተቋሙ የበላይ ከፍተኛ ሀላፊዎች እየተመራ በየቀኑ የሚካሄደው የኤዲቶሪያል ኮንፈረስም የሚሰሩ ዜናዎች እና ፕሮግራሞችን የሚያፀድቀው ዋናው የአሰራር መርሆው ከአለም አቀፍ የሙያ መርሆና ተግባሮት ተቀድቶ በተዘጋጀ የኤዲቶሪል ፖሊሲ ነው
- ❖ የሚዲያው ዜና ማዕከሉ በተለይ ከተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የይዘት መፍለቂያ ቦታ ከመላው አገሪቱ እንዲሁም የአሰራር እና የይዘት ብዝሃነት መካተቱን ከግምት ውስጥ አሰገብቶ ይሰራል
- ❖ መስፈርቶችን ያሟሉ ይዘቶች ተመርጠው እና ተመርተው ለአየር ይበቃሉ

አንዳንድ የይዘት ስራዎች መስፈርቶችን አሟልተው እያለ እንኳን የሀብት ፍታሀዊ ክፍፍሉን ለማሰፈን ሲባል ቋንቋዎችና ቻናሎች መሰረት ያደረገ የኤዲቶሪያል ውሳኔዎች ተግባራዊ

**ይደረጋል፡፡ የአሰራር ሥርዓቱ** (Process Description) **ስዕላዊ መግለጫ በአባሪ** 8 **ተያይዟል፡፡**

# ክፍል ሁለት
# ግኝቶች

## I. የኮርፖሬሽኑ የስራ አመራር ቦርድ ኮርፖሬሽኑን በብቃት ለመምራት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፤

### የስራ አመራር ቦርዱ የራሱ የሆነ የአሰራር መመሪያ ማውጣቱን በተመለከተ

29. የኮርፖሬሽኑ የስራ አመራር ቦርድ የራሱ የሆነ የአሰራር መመሪያ ሊያወጣ ይገባል፡፡
30. የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽንን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 1278/2015 አንቀፅ 8/6 መሰረት ቦርዱ የራሱን የአሰራር መመሪያ እንደሚያወጣ ይገልፃል፡፡
31. ይሁን እንጂ የኮርፖሬሽኑ የስራ አመራር ቦርድ ስራዎችን ለመምራት የሚያስችለውን የራሱ የሆነ የአሰራር መመሪያ የሌለው እና ያላወጣ መሆኑን ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ለስራ አመራር ቦርዱ ሰብሳቢ ከቀረበ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡
32. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ የስራ አመራር ቦርዱ ስራውን የሚመራበት የራሱ የፀደቀ ውስጠ ደንብ ያለው መሆኑን ገልፀዋል፡፡
33. የኮርፖሬሽኑ የበላይ የስራ ሃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ አለ የተባለው መመሪያ የቦርዱ የስብሰባ መመሪያ እንጂ ቦርዱ በአዋጁ የተሰጡትን ተግባራት ለመወጣት ስራዎችን ለመስራት የሚያስችለው የራሱ የሆነ የአሰራር መመሪያ ባለመሆኑ እንዲሁም በኮርፖሬሽኑ የ2013 - 2017 ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ገፅ 44 ቦርዱ የራሱ የስራ መመሪያ እንደሚያወጣ ቢያስቀምጥም ከዚህ አንፃር የተዘጋጀ መመሪያ የሌለው በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ሙሉ በሙሉ ለመቀበል ያዳግታል፡፡
34. በመሆኑም የስራ አመራር ቦርዱ በአዋጁ የተሰጡትን ዝርዝር ተግባራት ለመወጣት ስራዎችን ለመስራትና ለመከታተል እንዳይችል አድርጓል፡፡

### የስራ አመራር ቦርዱ የመገናኛ ብዙሃንን በሚመለከት የወጡ የመንግስት ፖሊሲዎች እና ህጎች በኮርፖሬሽኑ ተግባራዊ መደረጋቸውን ማረጋገጡን በተመለከተ

35. የኮርፖሬሽኑ የስራ አመራር ቦርድ የመገናኛ ብዙሃንን በሚመለከት የመንግስት ፖሊሲዎች እና ህጎች በኮርፖሬሽኑ ተግባራዊ መሆናቸውን የሚያረጋገጥበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

36. የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽንን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 1278/2015 አንቀፅ 9/1 በተደነገገው መሰረት ቦርዱ የመገናኛ ብዙሃንን በሚመለከት የመንግስት ፖሊሲዎች እና ህጎች በኮርፖሬሽኑ ተግባራዊ መሆናቸውን ማረጋገጥ እንዳለበት ይገልፃል፡፡

37. ይሁን እንጂ ቦርዱ ይህ ስለመከናወኑ የሚያረጋገጥበት የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑን፣ በተጨማሪም ቦርዱ ክትትል የሚያደርገው ኮርፖሬሽኑ በሚያቀርባቸው የአፈፃፀምና የክትትል ሪፖርቶች ላይ ቦርዱ አስተያየት በመስጠት እና ኮርፖሬሽኑን የሚገመግመው በሚያቀርብለት ስትራቴጅክ እና አመታዊ እቅድ መሆኑን የቦርዱ ሰብሳቢ በኦዲቱ ወቅት ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

38. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ቦርዱ ይህንን ስራ የሚከታተለው የቦርዱ ውስጠ ደንብ የተቋሙን ኤዲቶሪያል ፖሊሲውን እና ሌሎች የመገናኛ ብዙሃን ህጎችን መሰረት በማድረግ መሆኑን እና ቦርዱ ለዚህ ራሱን የቻለ የአሰራር ማንዋል እንደሚያዘጋጅ በአዋጁ ያልተደነገገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

39. የኮርፖሬሽኑ የበላይ የስራ ሃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መልስ ላይ ይህን ይበሉ እንጂ የቦርዱ ውስጥ ደንብ ስለ ቦርዱ የስብስባ ሂደትና የቦርዱ አባላት ስነ ምግባርን የሚመለከት እንጂ የመገናኛ ብዙሃንን በሚመለከት የመንግስት ፖሊሲዎች እና ህጎች በኮርፖሬሽኑ ተግባራዊ መሆናቸውን የሚያረጋግጥበት መመሪያ አለመሆኑ፣ እንዲሁም ይህ ተግባር ስለመከናወኑ የቦርዱ የስብሰባ ቃለ ጉባኤ በተከለሰበት ወቅት ማስረጃ ማግኘት ያልተቻለ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ እንደምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

40. በመሆኑም ቦርዱ የመገናኛ ብዙሃንን በሚመለከት የመንግስት ፖሊሲዎችን እና ህጎችን በኮርፖሬሽኑ ተግባራዊ መሆናቸውን የመከታተል እና የመቆጣጠር ስራ የሚያከናውን ስለመሆኑ ማረጋገጥ አያስችልም፡፡

## የስራ አመራር ቦርዱ በኮርፖሬሽኑ የሚቀርቡ ፕሮግራሞች የሃሳብና የይዘት ብዝሃነት ያላቸው መሆናቸውን መከታተሉን በተመለከተ

41. የኮርፖሬሽኑ የስራ አመራር ቦርድ በኮርፖሬሽኑ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ሚዲያዎች የሃሳብና የይዘት ብዝሃነት ያላቸው ፕሮግራሞች ተቀርፀው ለህዝብ መቅረባቸውን የሚከታተልበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

42. የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽንን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 1278/2015 አንቀፅ 9/4 በተደነገገው መሰረት ቦርዱ በኮርፖሬሽኑ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ሚዲያዎች የሃሳብና የይዘት ብዝሃነት ያላቸው ፕሮግራሞች ተቀርፀው ለህዝብ መቅረባቸውን መከታተል እንዳለበት ይገልፃል፡፡

43. ይሁን እንጂ ቦርዱ በኮርፖሬሽኑ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ሚዲያዎች የሃሳብና የይዘት ብዝሃነት ያላቸው ፕሮግራሞች ተቀርፀው ለህዝብ መቅረባቸውን የሚከታተለበት ራሱን የቻለ የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፤ እንዲሁም ቦርዱ ክትትል የሚያደርገው በኮርፖሬሽኑ ስትራቴጅክ እቅድ እንዲኖር በማድረግና የኮርፖሬሽኑን አመታዊ እቅድና አፈፃፀም በመገምገም መሆኑን ለስራ አመራር ቦርዱ ሰብሳቢ ከቀረበ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

44. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የኮርፖሬሽኑ የበላይ የስራ ሃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ቦርዱ የተቋሙን ሪፖርት ከመገምገም ባለፈ ከብዝሃነት አንጻር የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚያነሱትን ጥያቄ መሰረት በማድረግ ተቋሙን ይገመግማል ብዙሃነት በተቋሙ እንዲሰፍን አቅጣጫ እንደሚሰጥ ገልፀዋል፡፡

45. የኮርፖሬሽኑ የበላይ የስራ ሃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ ከቦርዱ ቃለ ጉባኤ ለማወቅ እንደተቻለው ከ2013 - 2015 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ቦርዱ የኮርፖሬሽኑን የስራ አፈፃፀም ማለትም የይዘት ዘርፉን የገመገመው በ2015 ዓ.ም ሁለት ጊዜ ብቻ እና በ2013 ዓ.ም አንድ(1) ጊዜ ብቻ መሆኑን እንዲሁም ሌሎች የስራ አመራር የስብሰባ ቃለ ጉባኤዎቹ አጀንዳ የሚካተቱት ስለተቋሙ መዋቅር ማሻሻያ እንጂ በኮርፖሬሽኑ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ሚዲያዎች የሃሳብና የይዘት ብዝሃነት ያላቸው ፕሮግራሞች ተቀርፀው ለህዝብ ስለመቅረባቸው ስለተደረገ ክትትል ባለመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

46. በመሆኑም ቦርዱ በኮርፖሬሽኑ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ሚዲያዎች የሃሳብና የይዘት ብዝሃነት ያላቸው ፕሮግራሞች ተቀርፀው ለህዝብ መቅረባቸውን ክትትል እንዳያደርግ ያደርገዋል፡፡

## የስራ አመራር ቦርዱ ኮርፖሬሽኑ በሚሰጠው አገልግሎት ህዝቡ ተጠቃሚ መሆኑን የሚገመግምበት የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ

47. ቦርዱ ኮርፖሬሽኑ በሚሰጠው አገልግሎት ህዝቡ ተጠቃሚ መሆኑን የሚገመግምበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
48. የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽንን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 1278/2015 አንቀፅ9/5 በተደነገገው መሰረት ቦርዱ ኮርፖሬሽኑ በሚሰጠው አገልግሎት ህዝቡ ተጠቃሚ መሆኑን እንደሚገመግም ይገልፃል፡፡
49. ይሁን እንጂ ቦርዱ ኮርፖሬሽኑ በሚሰጠው አገልግሎት ህዝቡ ተጠቃሚ መሆኑን የሚገመግምበት የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ ለስራ አመራር ቦርዱ ሰብሳቢ ከቀረበ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡
50. እንዲሁም ቦርድ የራሱ የሆነ የክትትል ስርዓት የሌለውና ቦርዱ ክትትል የሚያደርገው ኮርፖሬሽኑ በሚያቀርባቸው የክትትል ስርዓቶች ላይ ቦርዱ አስተያየት በመስጠትና በሚቀርብለት ስትራቴጅክ እቅድ፣ አመታዊ እቅድ መሆኑን የቦርዱ ሰብሳቢ በቃለ መጠይቅ ወቅት አክለው ገልፀዋል፡፡
51. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የኮርፖሬሽኑ የበላይ የስራ ሃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ቦርዱ በስብሰባ ወቅት የአድማጭ ተመልካች አስተያየቶችን በሚመለከት ትኩረት ሰጥቶ እንደሚነጋገርና ተቋሙ የይዘት ጥራት ላይ ትኩረት እንዲያደርግ የተቋሙን አቅም ባገናዘበ መልኩ በየክልሉ ስቱዲዮዎች እንዲከፈቱ አቅጣጫ በመስጠት እና ኢ.ቢ.ሲ ኢትዮጲያን እንዲመስል በሚሰጠው የስራ አቅጣጫ የህዝቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እየሰራ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡
52. የኮርፖሬሽኑ የበላይ የስራ ሃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ ከቦርዱ ቃለ ጉባኤ ለመረዳት እንደታቻለው የስራ አመራር ቦርዱ በስብሰባ ወቅት አብዛኛውን ጊዜ ውይይት የሚያደርገው በተቋሙ አስተዳደራዊ ስራዎች ላይ እንጂ ኮርፖሬሽኑ በሚሰጠው አገልግሎት ህዝቡ ተጠቃሚ መሆኑን የገመገመበት ሁኔታ አለመኖሩን ከቦርዱ ቃለ ጉባኤ ለማወቅ የተቻለ በመሆኑ እና ከላይ በምላሻቸው በተጠቀሰው አግባብ ስለመሰራቱ ማስረጃው ለኦዲቱ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡
53. በመሆኑም ቦርዱ ኮርፖሬሽኑ በሚሰጠው አገልግሎት ህዝቡ ተጠቃሚ መሆኑን የማይገመግም በመሆኑ በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት እንዳይወጣ አድርጓል፡፡

### የስራ አመራር ቦርዱ ኮርፖሬሽኑ ሚዛናዊ የሆነ የራዴዮና የቴሌቪዥን አገልግሎት መስጠቱን መከታተሉን በተመለከተ

54. ቦርዱ የተለያየ አመለካከት ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶችና የህብረተሰብ ክፍሎች ሚዛናዊ የሆነ የራዴዮና የቴሌቪዥን ፍትሃዊ አገልግሎት ማግኘታቸውን የሚከታተልበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
55. የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽንን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 1278/2015 አንቀፅ 9/6 በተደነገገው መሰረት ቦርዱ የተለያየ አመለካከት ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶችና የህብረተሰብ ክፍሎች ሚዛናዊ የሆነ የራዴዮና የቴሌቪዥን ፍትሃዊ አገልግሎት ማግኘታቸውን እንደሚከታተል ይገልፃል፡፡
56. ይሁን እንጂ ቦርዱ የተለያየ አመለካከት ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶችና የህብረተሰብ ክፍሎች ሚዛናዊ የሆነ የራዴዮና የቴሌቪዥን ፍትሃዊ አገልግሎት ማግኘታቸውን የሚከታተልበት የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ እና ቦርድ የራሱ የሆነ የክትትል ስርዓት የሌለው መሆኑን፣ ነገር ግን ቦርዱ ኮርፖሬሽኑን የሚገመግመው በሚያቀርብለት ስትራቴጅክ እቅድና አመታዊ እቅድ መሰረት መሆኑን ለስራ አመራር ቦርዱ ሰብሳቢ ከቀረበ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡
57. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የኮርፖሬሽኑ የበላይ የስራ ሃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ በዋናነት ቦርዱ ይህንን ስራ የሚሰራው የኤዲቶሪያል ፖሊሲውን መሰረት በማድረግ እንደሆነና ከቦርዱ አወቃቀር ጀምሮ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች የቦርዱ አባል ሆነው የተመደቡ መሆኑንና እነዚህ የቦርዱ አባላት የተፎካካሪ ፓርቲ ሃሳቦች በኮርፖሬሽኑ ሚዲየሞች በአግባቡ መሄዱን በማረጋገጥ የተቋሙን ሪፖርት ማፅደቃቸውን የሃሳብ ብዙሃነትን ማስተናገጃ ማሳያ ነው ሲሉ ገልፀዋል፡፡
58. የኮርፖሬሽኑ የበላይ የስራ ሃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በሰኔ 2015 ዓ.ም የኢቢሲ ተቋማዊ ሪፎርም የማፅናት ምዕራፍ ሰነድ ላይ ለተፎካካሪ ፓርቲዎች የሚሰጠው ጊዜ አናሳ መሆኑ እንዲሁም የተለየ ሀሳብ ያላቸው የሲቪል ማህበራትና የሙያ ማህበራት ሚዲያው ተገቢ ትኩረት የማይሰጣቸው መሆኑን የተገለፀ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ እንደምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡
59. በመሆኑም ቦርዱ የተለያየ አመለካከት ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶችና የህብረተሰብ ክፍሎች በኮርፖሬሽኑ ሚዛናዊ የሆነ የራዴዮና የቴሌቪዥን ፍትሃዊ አገልግሎት ማግኘታቸውን እንዳይረጋገጥ አድርጓል፡፡

**የስራ አመራር ቦርዱ የፕሮግራም ይዘት የሚገመግምበትና ስለሚሻሻልበት ሁኔታ ሃሳብ ማቅረቡን በተመለከተ**

60. ቦርዱ በራዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በዲጅታል ሚዲያ እና በሌሎች ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች የሚተላለፈውን የፕሮግራም ይዘት የሚገመግምበትና ስለሚሻሻልበት ሁኔታ ሃሳብ የሚያቀርብበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

61. የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽንን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 1278/2015 አንቀፅ 9/7 በተደነገገው መሰረት ቦርዱ በራዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በዲጅታል ሚዲያ እና በሌሎች ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች የሚተላለፈውን የፕሮግራም ይዘት የሚገመግምበትና ስለሚሻሻልበት ሁኔታ ሃሳብ እንደሚያቀርብ ይገልፃል፡፡

62. ይሁን እንጂ ቦርዱ በራዲዮ፣ በቴሌቪዥን ፣በዲጅታል ሚዲያ እና በሌሎች ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች የሚተላለፈውን የፕሮግራም ይዘት የሚገመግምበትና ስለሚሻሻልበት ሁኔታ ሃሳብ የሚያቀርብበት የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑን፣ ነገር ግን ቦርዱ ኮርፖሬሽኑን የሚገመግመው በሚያቀርብለት ስትራቴጅክ እቅድና አመታዊ እቅድ መሰረት መሆኑን ለስራ አመራር ቦርዱ ሰብሳቢ ከቀረበ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

63. እንዲሁም በኮርፖሬሽኑ የ2013-2017ዓ.ም ስትራቴጂያዊ ዕቅድ የስራ አመራር ቦርዱ ይዘቶችን የመገምገምና ኮርፖሬሽኑን የማሻሻል ስራ እንደሚጠበቅበት የተገለፀ ሲሆን፤ ኮርፖሬሽኑን ወደ ተሻለ ምዕራፍ ሊያሸጋግሩ የሚችሉ እቅዶችን አቅዶ መስራት የሚገባው መሆኑን የተገለፀ መሆኑ፤ የተቋሙን ጊዜያዊና ዘላቂ ችግሮችን ለመቅረፍ በሚያስችል መልኩ ወቅቱን የጠበቀ ግንኙነት በማድረግ ረገድ ክፍተት እንዳለበት ተገልፃል።

64. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የኮርፖሬሽኑ የበላይ የስራ ሃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ቦርዱ ይህንን ስራ የሚሰራው የኮርፖሬሽንኑን ኤዲቶሪያል ፖሊሲ መሰረት በማድረግ እንደሆነ እንዲሁም ኢቢሲ ተግባራዊ ያደረገው እና በሀገር ደረጃ አነጋጋሪ የሆነው የኢቢሲ ሪፎርም በዋናነት የተመራው ቦርዱ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

65. የኮርፖሬሽኑ የበላይ የስራ ሃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ የስራ አመራር ቦርዱ በ2013 ዓ.ም አንድ (1) ጊዜ ፣ በ2014 ዓ.ም ሶስት (3) ጊዜ እና በ2015 ዓ.ም ደግሞ ሁለት(2) ጊዜ ብቻ የስራ አመራር ቦርዱ የተሰበሰበ መሆኑን ቦርዱ የስብሰባ ጊዜውን ጠብቆ ባልተሰበሰበበት እና ቦርዱ ሪፎርሙን ስለመምራቱ ማስረጃ ባለመቅረቡ፤ እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት ከቦርዱ ቃለ ጉባኤ ለመረዳት እንደታቻለው የስራአመራር ቦርዱ በስብሰባ ወቅት አብዛኛውን ጊዜ ውይይት የሚያደርገው በተቋሙ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ እንጂ

የፕሮግራም ይዘት ስለሚሻሻልበት ሁኔታ ስለመገምገሙ የሚያስረዳ አለመሆኑን ከቦርዱ ቃለ ጉባኤ ለማወቅ የተቻለ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

66. በመሆኑም ቦርዱ በራዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በዲጅታል ሚዲያ እና በሌሎች ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች የሚተላለፉትን ፕሮግሞች ይዘቱን የሚገመግምበትና ስለሚሻሻልበት ሁኔታ ሃሳብ የሚያቀርብበት ወጥነትና ቀጣይነት ያለው ስርዓት እንዳይኖር ያደርጋል፡፡

**የስራ አመራር ቦርዱ ከአድማጭ ተመልካቾች ቅሬታዎችን የሚመረምር እና ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን በተመለከተ**

67. ቦርዱ ከአድማጭ ተመልካቾች በኮርፖሬሽኑ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የሚመረምርበትና ተገቢውን ውሳኔ የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

68. የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽንን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 1278/2015 አንቀፅ 9/8 በተደነገገው መሰረት ቦርዱ ከአድማጭ ተመልካቾች በኮርፖሬሽኑ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን እንደሚመረምርና ተገቢውን ውሳኔ እንደሚሰጥ ይገልፃል፡፡

69. ይሁን እንጂ ቦርዱ ከአድማጭ ተመልካቾችን በኮርፖሬሽኑ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የሚመረምርበትና ተገቢውን ውሳኔ የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ ቢሆንም ቦርዱ በየሩብ አመቱ በኮርፖሬሽኑ የመጡ ቅሬታዎች ምንድን ናቸው ብሎ የሚያይ መሆኑን፣ ነገር ግን እስካሁን ድረስ ለቦርዱ ከአድማጭ ተመልካቾች የመጣ ቅሬታ አለመኖሩን የቦርዱ ሰብሳቢ በቃለ መጠይቅ ወቅት ገልፀዋል፡፡

70. እንዲሁም በኮርፖሬሽኑ በየወሩ በሚያቀርባቸው የአድማጭ ተመልካቾች ቅሬታ ሪፖርቶች ውስጥ የሬዲዮ ስርጭት ጥራት ችግርና ተደራሽነት ላይ በተደጋጋሚ ከህዝብ የሚነሱ ቅሬታዎች ያሉ ቢሆኑም ችግሮቹን እንዲፈቱ ያላደረገ መሆኑን ከቀረቡት ሪፖርቶች ለመረዳት ተችሏል፡፡ **ለማሳያ ያህል ቅሬታዎች በአባሪ 3 ተያይዟል**

71. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የኮርፖሬሽኑ የበላይ የስራ ሃላፊዎች ተጠይቀው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ቦርዱ የተቋሙን ስራ የሚመራው የቦርዱን ውስጠ ደንብ እና የተቋሙን ኤደቶሪያል ፖሊሲ መሰረት በማድረግ ሲሆን የአድማጭ ተመልካች ጥያቄዎች ሲመጣም የኤዲቶሪያል ፖሊሲውን መሰረት በማድረግ ምላሽ እንደሚሰጥ እንዲሁም ኮርፖሬሽኑ ከአድማጭ ተመልካቹ ለሚመጡ ቅሬታዎች በወቅቱ ምላሽ ስለመስጠቱ ከኢትዮጲያ መገናኛ ብዙሃን ባለስልጣን ማረጋገጥ እንደሚቻል ገልፀዋል፡፡

72. የኮርፖሬሽኑ የበላይ የስራ ሃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በየጊዜው የሚመጡ የአድማጭ ተመልካች ቅሬታዎች እየተፈቱ አለመሆኑን በየወሩ ከሚቀርቡት ከአድማጭ ተመልካች

ሪፖርት መረዳት የሚቻል በመሆኑ፣ እንዲሁም በየጊዜው ከአድማጭ ተመልካች የሚቀርቡ ቅሬታዎች ተመሳሳይነት ያላቸው በመሆኑና ይህም ቦርዱ ትኩረት ሰጥቶ የአድማጭ ተመልካቾች ቅሬታዎችን ግምገማ በማድረግ የውሳኔ ሃሳብ እየሰጠ አለመሆኑን የሚያስረዳ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

73. በመሆኑንም ቦርዱ ከአድማጭ ተመልካቾች በኮርፖሬሽኑ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በአግባቡ በመለየት የመፍትሄ አቅጣጫ እንዳይሰጥ ያደርገዋል፡፡

**የስራ አመራር ቦርዱ የኮርፖሬሽኑን የሚያቀርባቸው ፕሮግራሞች ተደራሽ መሆናቸውን መከታተሉን በተመለከተ**

74. ቦርዱ የኮርፖሬሽኑን ፕሮግራሞች በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ተደራሽ መሆናቸውን የሚከታተልበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

75. የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽንን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 1278/2015 አንቀፅ 9/10 በተደነገገው መሰረት ቦርዱ የኮርፖሬሽኑን ፕሮግራሞች በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ተደራሽ መሆናቸውን እንደሚከታተል ይገልፃል፡፡

76. ይሁን እንጂ ቦርዱ የኮርፖሬሽኑን ፕሮግራሞች በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ተደራሽ መሆናቸውን የሚከታተልበት አሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑን፣ ነገር ግን በሬዲዮ በሚተላለፉ ፕሮግራሞችና ዜናዎች ተደራሽ ባልሆነባቸው አካባቢዎችና የጥራት ችግር ባለባቸው አካባቢዎች ከኮርፖሬሽኑ በሚያቀርብለት ስትራቴጅክ እቅድና አመታዊ እቅድ ላይ እንዲሻሻሉ ትዕዛዝ የሚሰጥ መሆኑን ለስራ አመራር ቦርዱ ሰብሳቢ ከቀረበ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

77. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የኮርፖሬሽኑ የበላይ የስራ ሃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ከአድማጭ ተመልካቹ በ 982 የስልክ መስመር ከሁሉም የሃገሪቱ ክፍሎች ከሚቀርቡለት አስተያየት እንዲሁም የኮርፖሬሽኑ ስልጠና እና ጥናት ዘርፍ በሚያጠናው ጥናት ተከትሎ የማሰራጫ ጣቢያዎች ማሻሻያ ፕሮጀክት እንዲተገበር ቦርዱ አቅጣጫ እንደሚያስቀምጥ ገልፀዋል፡፡

78. የኮርፖሬሽኑ የበላይ የስራ ሃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ አብዛኛዎቹ የሬዲዮ የማሰራጫ ጣቢያዎች ካላቸው የማሰራጨት አቅም ከ50% በታች በሆነ መልኩ እያስተላለፉ የሚገኙ መሆኑ እንዲሁም ችግሮቹን ለመፍታት የተላለፉ ውሳኔዎችና የተሰሩ ሥራዎች ለኦዲት ያልቀረበ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

79. በመሆኑም ቦርዱ የኮርፖሬሽኑን ፕሮግራሞች በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ተደራሽ መሆናቸውን የሚከታተልበት አሰራር ስርዓት ባለመኖሩ በኮርፖሬሽኑ የሚተላለፉ ፕሮግራሞች ተደራሽ ባልሆነባቸውና የጥራት ችግር ያለባቸው አካባቢዎች በቀላሉ ለማወቅና የማስተካከያ እርምጃ ለመውስድ እንዳይችል ያደርገዋል፡፡

**የኮርፖሬሽኑ የስራ አመራር ቦርድ አመራር የስብሰባ ጊዜን በተመለከተ**

80. የኮርፖሬሽኑ ስራ አመራር ቦርድ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

81. የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽንን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 1278/2015 አንቀፅ 10/1 በተደነገገው መሰረት የኮርፖሬሽኑ ቦርድ አመራር ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ እንደሚሰበሰብ ይገልፃል፡፡

82. ይሁን እንጂ የኮርፖሬሽኑ ስራ አመራር ቦርድ ወቅቱን ጠብቆ ስብሰባውን የማያካሄድ መሆኑን፣ እንዲሁም ቦርዱ በ2013 ዓ.ም አንድ (1) ጊዜ ፣ በ2014 ዓ.ም ሶስት(3) ጊዜ እና በ2015 ዓ.ም ደግሞ ሁለት(2) ጊዜ ብቻ የስራ አመራር ቦርዱ የተሰበሰበ መሆኑን ከቦርዱ የስብሰባ ቃለ ጉባኤ ለማወቅ ተችሏል፡፡

83. በተጨማሪም የቦርዱ ሰብሳቢ በኦዲቱ ወቅት ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ቦርዱ እንደየሁኔታው እና በአጀንዳዎች ሁኔታ አሳሳቢነት የሚሰበሰብ መሆኑንና ቢያንስ በ3 ወር ስብሰባውን የሚያደርግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

84. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የኮርፖሬሽኑ የበላይ የስራ ሃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ከወቅቱ ሀገራዊ ሁኔታ አንፃር ቦርዱ ወቅቱን ጠብቆ መሰብሰብ ባይቻልም የቦርዱ ሰብሳቢ ከተቋሙ የበላይ ሃላፊ ጋር በመነጋገር የስራ አቅጣጫ የሚሰጥበትን አካሄድ እንደሚከተል ገልጸዋል፡፡

85. በመሆኑም ቦርዱ ይዘቶችን የመገምገምና ኮርፖሬሽኑን የማሻሻል ስራ እና የተቋሙን ጊዜያዊና ዘላቂ ችግሮችን ለመቅረፍ በሚያስችል መልኩ ወቅቱን የጠበቀ ግንኙነት በማድረግ ረገድ ክፍተት እንዲፈጠር አድርጓል፡፡

## II. ኮርፖሬሽኑ የሬዲዮና የቴሌቪዥን የዜና አገልግሎትን በብቃት ለመስጠት የሚያስችል መመሪያ፣ ስታንዳርድ እና የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ

### ኮርፖሬሽኑ የኦዶቪዥዋል አርካይቭ ዲጂታላይዝ ማደረጉን በተመለከተ

86. ኮርፖሬሽኑ የኦዶቪዝዋል አርካይቭ ዲጂታላይዝ በማድረግ መረጃዎችን ሊይዝ ይገባል፡፡
87. ኦዲዮቪዥዋል ከወረቀት በተሻለ መልኩ አሳማኝና እውነታን የያዘ መረጃ ቢሆንም ለብልሽት፣ለብክነትና ለውድመት በጣም የተጋለጠ ነው። በመሆኑም ኮርፖሬሽኑ ለተጠቀሱት የአርካይቭ ሃብት አያያዝ ችግሮች መፍትሄ ሊሆን የሚችል፣ ሰፊና ሁለገብ የኦዲዮቪዥዋል አርካይቭ ፖሊሲ በመቅረጽና ፖሊሲው ሊያስፈጽም የሚችል አስፈጻሚ አካል በመመደብ እንደሚያደራጅ በኮርፖሬሽኑ የኢዲቶሪያል ፖሊሲ ገፅ 114 ተገልፆል፡፡
88. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለመረዳት እንደተቻለው፡- በመላ ኢትዮጵያ ድምጸችና ፊልሞች/ቪድዮዎች መቀረጽ ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ በኦዲዮ እና በኦድዮቪዥዋል የተቀረጹ ሰነዶች በሙሉ ለማለት በሚቻልበት ሁኔታ የሚገኙት እና ይህ ደግሞ ተቋሙ በድምጽና ፊልም-ቪድዮ ተመዝግቦ የሚገኘውን የአገሪቷን ታሪክ ሙሉ በሙሉ የያዘ ብቸኛ ተቋም መሆኑ በኤዲቶሪያል ፖሊሲው ላይ የተገለፀ ቢሆንም፤

- የቴሌቪዥን አርካይቭን እስከ ህዳር 3/3/2016 ዓ.ም ድረስ አስራ አራት ሺህ ሰዓት ብቻ ፋይል ዲጂታላይዝድ የተደረገ መሆኑ፣
- የቴሌቪዥን አርካይቭ እስከ አሁን ከአርባ ሺህ ሰዓት በላይ ፋይል ዲጂታላይዝድ ያልተደረገ መሆኑ፣
- በኮርፖሬሽኑ የ2013-2017 ዓ.ም ስትራቴጂካያዊ ዕቅድ ላይ እንደተገለፀው ለአመታት ያከማቻቸውን አለም አቀፍ እና ሃገራዊ ፋይዳ ያላቸው መረጃዎችን ወደ ዲጂታል በመቀየር ለይዘት ስራዎች ግብአት በመፍጠር እንዲሁም ሃብት ለማግኘት ፕሮጀክት ቢቀርፅም ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣
- እንዲሁም በኮርፖሬሽኑ የ2013-2017ዓ.ም ስትራቴጂካያዊ ዕቅድ ላይ እንደተገለፀው የዲጂታል አርካይቭ ሲሰተም አቅም ከፍ በማድረግ ደረጃውን በማሻሻል ተደራሽነቱን በማረጋገጥ እንዲሁም የዲጂታል አርካይቭ ሀብትን ለገቢ ምንጭነት መጠቀም እንዲቻል ቢታቀድም ከተወሰኑ የኒውስ ሩም፤ ኤዲቲንግ

ሲስተም ሶፍትዌር ማሻሻያ (upgrade) በስተቀር ሙሉ ለሙሉ በሚፈለገው ደረጃ ያልተከናወነ መሆኑን ከተከለሱ ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል ፡፡

89. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የቴክኖሎጂ ዘርፍ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በአርካይቭ ፖሊሲ መሰረት ኦዶቪዥዋል አርካይቮችን ወደ ዲጅታል አርካይቪ እየተቀየረ ስለሆነ ይህንን የሚመጥን መመሪያ እየተዘጋጀ መሆኑን፣ እንዲሁም የኮርፖሬሽኑ ፋይሎች ዲጅታላይዝ ያልተደረጉ መሆኑንና ይህም የሆነበት ምክንያት ማሽኖች በቀላሉ የማይገኙና ውድ በመሆናቸው ፋይሎችን ዲጅታላዝ ማድረግ እንዳልተቻለ ገልፀዋል፡፡

90. የኮርፖሬሽኑ የበላይ የስራ ሃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ኮርፖሬሽኑ አርካይቭን ዲጂታላዝ ለማድረግ የሚያስፈልጉ መገልበጫ ማሽኖች በሀገር ውስጥ ባለመኖራቸው ዲጂታላይዝ የማድረግ ሥራው የተቋረጠ ሲሆን በ2015 አጋማሽ ላይ ከፈረንሳይ ኤምባሲ ጋር የተፈራረሙትን ስምምነት ተከትሎ የ3000 ሰዓት አርካይቭ ዲጅታል ለማድረግ ስራዎች የተጀመረ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

91. የኮርፖሬሽኑ የበላይ የስራ ሃላፊዎች በመውጫ ስብሰባና በረቂቅ የሪፖርት መልስ ወቅት እንደገለፁት ኮርፖሬሽኑ የአርካይቭ ሀብትን ዲጅታላዝ ለማድረግ ከፍተኛ ችግር የሆነው በተለይም የድሮ ካሴቶች መገልበጫ ማሽን በሀገር ውስጥ አለመኖር ሲሆን ይህንን ማሽን በግዢ ወይም በኪራይ ለማግኘት እንዲቻል በጀት እንዲፈቀድ ለገንዘብ ሚኒስቴርና ለፕላን ሚኒስቴር ጥያቄ የቀረበ ቢሆንም የረቂቅ ሪፖርቱን መልስ እስከመለሱበት ሚያዚያ 11/2016 ዓ.ም ድረስ የበጀት ድጋፉ ያልተገኘ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

92. በመሆኑም ኮርፖሬሽኑ ያሉትን ፋይሎች ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ ለማስቀመጥና ለትውልድ ለማስተላለፍ እንዳይቻል ያደርገዋል፣ እንዲሁም አርካይቩ በተገቢው መንገድ ተጠብቆ የሰነድ ስርዓቱንና ለይዘት የሚሰጠውን አገልግሎት ብቁ እንዳይሆን ያደርገዋል።

### ኮርፖሬሽኑ የኤዲቶሪያል ፖሊሲውን መከለሱን በተመለከተ

93. ኮርፖሬሽኑ የሚዲያውን ኢንዱስትሪ እና የአገሪቱን የእድገት ሽግግር ከግምት ውስጥ በማስገባት የኤዲቶሪያል ፖሊሲው በየአምስት አመቱ ሊከለስ ይገባል ፡፡

94. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ ቃለመጠይቆች መሰረት ኢዲቶሪያል ፖሊሲው ከወጣ ከ10 አመት በላይ ቢሆንም ኮርፖሬሽኑ አንድም ጊዜ የሚዲያውን ኢንዱስትሪ እና የአገሪቱን የእድገት ሽግግር ከግምት ውስጥ በማስገባት የኢዲቶሪያል ፖሊሲው ያልከለሰ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

95. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የኮርፖሬሽኑ የስራ ሃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ኮርፖሬሽኑ የኤዲቶሪያል ፖሊሲውን ወቅቱን ጠብቆ ያልተሻለ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ኢዲቶርያል ፖሊሲውን ለማሻሻል ኮሚቴ ተቋቁሞ የመጀመሪያው ረቂቅ መጠናቀቁን እና ለኦዲት ቡድኑ ማስረጃውን እንዳቀረቡ ገልፀዋል፡፡

96. በመሆኑም ኮርፖሬሽኑ የኤዲቶሪያል ፖሊሲው ተጨባጭ ሁኔታዎችንና የሚደያ ኢንዱስትሪውን ለውጥና ዕድገት የሚጠይቀውን በማካተት በየአምስት አመቱ መከለስ እንዳለበት ቢቀመጥም የተደረገ ማሻሻያ ባለመኖሩ በየጊዜው ክፍተታቸውን እየፈተሹ ደረጃቸውን እንዲጠብቁም ሆነ የአሰራር ውጤታማነት እንዲያስገኙ የማድረግ ስራዎች ላይ ክፍተት እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡

## III. ኮርፖሬሽኑ የሬዲዮና ቴሌቪዥን የዜና አገልገሎት ሽፋንን፤ ተደራሽነትንና ስብጥርን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመስጠት የሚያስችለው የአሰራር ሥርአት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን መገምገምን በተመለከተ

### ኮርፖሬሽኑ ኤዲቶሪያል ነፃነት በተጠበቀ ከማንኛውም አካል ነፃና ገለልተኛ መሆኑን በተመለከተ

97. ኮርፖሬሽኑ ኤዲቶሪያል ነፃነት በተጠበቀ እና በሥራውም ሆነ በአስተዳደሩ መንግሥትና የመንግሥት ተቋማትን ጨምሮ ከማንኛውም አካል ነፃና ገለልተኛ ሊሆን ይገባል ፡፡

98. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ኮርፖሬሽኑ ከማንኛውም አካል ነፃና ገለልተኛ ሆኖ እየሰራ አለመሆኑን ከተከለሱ ሰነዶች እና ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ለማሳያ፤

- ኮርፖሬሽኑ የመንግስትን የመልካም አስተዳደር ችግር የሚያጋልጥ ዜና ወይም ፕሮግራም ከሰራ ለምን ተብሎ ከመንግስት አካላት ስልክ የሚደወል መሆኑ? መጋቢት 27/2015 ዓ.ም ከተካሄደው የስራ አመራር ቦርዱ የስብሰባ ቃለ ጉባኤ የተገለፀ መሆኑ፤
- በ2014 ዓ.ም የኮርፖሬሽኑ ፍኖተ ካርታ ላይ እንደተገለፀው የኮርፖሬሽኑ ዜናዎች ዋና ችግር በተቋሙ ውስጣዊና ውጫዊ ጫናዎች፣ ግለሰባዊና ፖለቲካዊ ግፊቶች የተነሳ አዲስ መረጃ ለሕዝብ ማቅረብ አለመቻሉ መገለፁ፤

➢ የመንግስት አስፈፃሚ አካላት በሚዲያው ላይ በሚያሳዩት ጣልቃ ገብነት በኮርፖሬሽኑ ላይ ተፅዕኖ እያሳደረ መሆኑ በኮርፖሬሽኑ ሥራ አመራር ቦርድ በነሀሴ 19/2015 ባደርገው ስብሰባ ቃለ ጉባኤ መገለፁ፣

➢ በሰኔ 2015 ዓ.ም የኢ.ቢ.ሲ ተቋማዊ ሪፎርም የማፅናት ምዕራፍ ሰነድ ላይ እንደተገለፀው ፡-

- ኮርፖሬሽኑ በሀገሪቱ የተፈጠሩ ጉዳዮችን በዝምታ በማለፍ ከቀናት በኃላ ችግሩ ተፈትቷል የሚሉ መሆኑ፤ እንዲሁም ህብረተሰቡ ከሌላ ምንጭ ቢሆንም መረጃውን ማግኘቱ ስለማይቀር ኢ.ቢ.ሲ ዝም ማለቱ ከህዝብ የሚለየው በመሆኑ ጥቅም እንደማይኖረው የተገለፀ መሆኑ መገለፁ፤
- የመንግስት ባለስልጣናት ሚዲያው የመንግስት ስኬታማ ስራዎችን ለህዝቡ እንዲያደርስ የሚፈልጉትን ያህል፤ጉድለቶችን እና ያልተሳኩ ክንውኖች ወደ ህዝቡ እንዲደርሱ ፍቃደኞች የማይሆኑ መሆኑ መገለፁ፤
- በሚዲያው የሚተላለፉ ዘገባዎች መነሻ የመንግስት ምላሽ እንጂ የህዝብ ቅሬታ ሲሆን የማይስተዋሉ መሆኑ መገለፁ የሚሉ ናቸው፡፡

99. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የኮርፖሬሽኑ የስራ ሃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ኮርፖሬሽኑ በተቋቋመበት አዋጅ መሰረት የመንግስትን ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ለህዝቡ የማድረስ እና የማስተዋወቅ ሃላፊነት ያለበት በመሆኑ ይህንን ሃላፊነት ለመወጣት በመንግስት አቅጣጫ መሰረት እንደሚሰራ፣ ከኤዲቶሪያል ነፃነት አንፃር የተሰጠው አስተያየት መሰረት ያደረገው ኮርፖሬሽኑ በ2014 የሪፎርም እቅዱን ሲያዘጋጅ ከለያቸው ችግሮች ውስጥ አንዱ የመንግስት ጫና ነው የሚል ነው እንጂ አሁን የመንግስት ጫና አለበት በሚል አግባብ አለመሆኑንና የቦርዱ ቃለጉባኤ ገፅ 3 ላይ በግልፅ እንደተቀመጠው ኮርፓሬሽኑ በሪፎርም የመፍታት ምዕራፍ እንደችግር ለይቷቸው በመቀየር ምዕራፍ እየሰራባቸው ያሉ ተግባራት መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

100. የኮርፖሬሽኑ የበላይ የስራ ሃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በ2015ዓ.ም የኢ.ቢ.ሲ ተቋማዊ ሪፎርም የማፅናት ምዕራፍ ላይ የመንግስት ጣልቃ ገብነት እንዳለ የሚገለፅ ሲሆን እንዲሁም ቦርዱ መጋቢት 2015ዓ.ም ባደረገው ስብሳባ ቃለ ጉባኤ ላይ ለመረዳት እንደተቻለው ኮርፖሬሽኑ የመንግስትን የመልካም አስተዳደር ችግር የሚያጋልጥ ዜና ወይም ፕሮግራም ከተሰራ ለምን ተብሎ ከመንግስት አካላት ስልክ የሚደወል መሆኑ በግልፅ የተጠቀሰ በመሆኑ፤ እንዲሁም የኮርፖሬሽኑ ሥራ አመራር ቦርድ በቀን

ነሀሴ19/2015 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ለማወቅ እንደተቻለው የመንግስት አስፈፃሚ አካላት በሚዲያው ላይ በሚያሳዩት ጣልቃ ገብነት በኮርፖሬሽኑ ላይ ተፅዕኖ እያሳደረ መሆኑ በግልፅ የተቀመጠበት ሁኔታ ያለ በመሆኑ ከሪፎርሙ በኋላ በ2015 ዓ. መጨረሻ ድረስ የቀጠለ በመሆኑ አሁን ላይ የመንግስት ጫና የለም ተብሎ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

101. በመሆኑም ኮርፖሬሽኑ ኤዲቶሪያል ነፃነት በተጠበቀ እና በሥራውም ሆነ በአስተዳደሩ መንግሥትና የመንግሥት ተቋማትን ጨምሮ ከማንኛውም አካል ነፃና ገለልተኛ ሆኖ ባለመስራቱ ህዝቡ የሚፈልገውን ሚዛናዊ መረጃ እንዳያገኙ ከማድረጉም በላይ ታማኝ የመረጃ ምንጭ የመሆን ተቀባይነቱን እንዲያጣ ያደርገዋል፡፡

### ኮርፖሬሽኑ በቋንቋዎች የሚያሰራጫቸው ስርጭቶች ሽፋንን በተመለከተ

102. ኮርፖሬሽኑ በቋንቋዎች ከሚያሰራጫቸው ስርጭቶች እስከ 70% ሽፋናቸው በክልሎች በሚከናወኑ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸው የተሞክሮ ልውውጥ ሊደረግባቸው በሚገቡ ጉዳዮች ላይ በማዕከል ላይ ደግሞ 30% ትኩረት አደርጎ ሊሰራ ይገባል::

103. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተሰለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ ቃለመጠይቶች ኮርፖሬሽኑ በቋንቋዎች ከሚያሰራጫቸው የዜና ይዘቶች 70% በክልል 30% በማዕከል አድርጎ እየሰራ አለመሆኑንና ኮርፖሬሽኑ በቋንቋዎች ከሚያሰራጫቸው ይዘቶች አብዛኛዎቹ ከማዕከል አካባቢ መሆኑ፣ እንዲሁም የቋንቋዎች ዜናና ወቅታዊ ጉዳዮች ዲቪዥን የሰው ሀይል እና የሚፈልገው ስራ በጣም ሰፊ ልዩነት ያለው መሆኑ መገለፁ፣ በተጨማሪም የቋንቋዎች ዜናና ወቅታዊ ጉዳዮች ዲቪዥን በመዋቅር መሰረት የሚፈልገው የሰው ሀይል ብዛት 244 ሲሆን እስከ የካቲት 2016 ዓ.ም ያለው የሰው ሀይል 81 ብቻ ሲሆን ከተፈቀደው መዋቅር አንፃር 33% ብቻ የተሟላ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

104. በተጨማሪም ፡-

- ኮርፖሬሽኑ በቋንቋዎች የሚያሰራጫቸው ይዘቶች የ2013 ዓ.ም እና የ2014 ዓ.ም በማዕከልና በክልል የተላለፉትን ዜናዎች በእቅድ አፈፃፀሙ ላይ በቁጥር ደረጃ ያልተቀመጠ መሆኑ፣
- ኮርፖሬሽኑ በቋንቋዎች ከሚያሰራጫቸው ይዘቶች አብዛኛዎች ከማዕከል አካባቢ መሆኑን ማለትም የፌዴራል ዜና የተዘገበው 30 በመቶ መሆን ሲገባው 42.9 በመቶ መሆኑ እና የክልል ዜና 70 በመቶ መሆን ሲገባው 57.1 በመቶ መሆኑ ታውቋል፡፡

105. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የኮርፖሬሽኑ የስራ ሃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ በኮርፖሬሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1278/2015 አንቀፅ 5 እና 6 መሰረት ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመበት ዋና አላማ በህዝቦች መካከል በመተማመን ላይ ያተኮረ አንድነት እንዲጠናከር መስራት እና ለዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ የበኩሉን የስርአት ግንባታ ሚና መጫወት እንደሆነ በግልፅ የተደነገገ ሲሆን፣ የክልሎች ጉዳይ በዋናነት የሚሸፈነው በክልል ሚዲያዎች እንደሆነና የኢቢሲ ሚና ክልሎችን እርስ በእርስ በማስተሳሰር እና በመግባባት ላይ የተመሰረተ ጠንካራ የጋራ ሀገር መገንባት ላይ ያተኮረ መሆኑንና በዚህም ምክንያት ኤዲቶሪያል ፖሊሲውን ከዚህ አንፃር ለማሻሻል ረቂቅ የተዘጋጀ እንደሆነና ፖሊሲው ከአዋጁ በላይ ስላልሆነ የተቋሙን አዋጅ ተከትሎ በመስራት ላይ እንደሚገኝ፣ እንዲሁም የቋንቋዎችን የሰው ሃይል ለማሞላት በርካታ ስራ እየተሰራ ሲሆን በአዲስ አበባ የሰው ሃይል ማግኘት ባልተቻለባቸው ቋንቋዎች /አፋር እና ሱማሊኛ/ ቋንቋ ላይ ክልል ድረስ በመሄድ ለመቅጠር ጥረት እንደተደረገ፣ በሌላ በኩል በመዋቅር የተያዘው መደብ የበጀት ጉዳይ ስላለበት በሙሉ በአንድ ጊዜ የሚሞላ እንዳልሆነ ገልፀዋል፡፡

106. በመሆኑም ኮርፖሬሽኑ በቋንቋዎች ከሚያሰራጫቸው ስርጭቶች ሽፋናቸው በብዛት ከማእከል የሚከናወኑ ሁነቶችና ፕሮጀክቶች ስለሆኑ በክልሎች በሚከናወኑ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸውና መልካም ተሞክሮዎች ላይ ሌሎች ክልሎች የልምድ ልውውጥና ትምህርት እንዳይወስዱ ያደርጋል፡፡

## ኮርፖሬሽኑ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ወይም ድርጅቶችን በፍትሃዊነት የሚያገለግልበት የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ

107. ኮርፖሬሽኑ በአገሪቱ ሕገ መንግሥትና የምርጫ ሕግ መሠረት የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ወይም ድርጅቶችን በፍትሃዊነት የሚያገለግልበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

108. የመገናኛ ብዙሀን አዋጅ ቁጥር 1238/2021 አንቀፅ 56/1ረ እና የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ኢዲቶሪያል ፖሊሲ ገፅ 30 እንደተገለፀው ኮርፖሬሽኑ በአገሪቱ ሕገ መንግሥትና የምርጫ ሕግ መሠረት የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ወይም ድርጅቶችን በፍትሃዊነት የሚያገለግልበት የአሰራር ስርዓት እንደሚዘረጋ ይገልፃል ፡፡

109. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ኮርፖሬሽኑ በአገሪቱ ሕገ መንግሥትና የምርጫ ሕግ መሠረት የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ወይም ድርጅቶችን በፍትሃዊነት የማያገለግል መሆኑ፡- ለማሳያ ያህል

- ኮርፖሬሽኑ የፖለቲካ ፓርቲዎችን በፍትሀዊነት የሚገለገሉበት በቂ መድረኮች የሌሉ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከቀረበ በቃለ መጠይቅ የተገኘ መሆኑ፣
- የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚያወጧቸው መግለጫዎች ግጭት ቀስቃሽ ናቸው በማለት የዘገባ ሽፋን የማያገኙ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከቀረበ በቃለ መጠይቅ የተገኘ መሆኑ፣
- ኢዜማ የሚያወጣቸው መግለጫዎችን በርካቶቹን ለኮርፖሬሽኑ በኢሜይል አድራሻ የላከ ቢሆንም አብዛኞቹን መግለጫዎች ለህዝብ ሳያደርስ የቀረ መሆኑን ኢዜማ በቃለ መጠይቅ ወቅት የገለፀ መሆኑ፤ **ለምሳሌ ያህል ኢዜማ ካወጣቸው መግለጫዎች በኮርፖሬሽኑ የዘገባ ሽፋን የሰጣቸውና ያልሰጣቸውን መግለጫዎች በአባሪ 6 ታያይዟዋል፡፡**
- በኮርፖሬሽኑ ከተሰጠው የዘገባ ሽፋን ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ የገገርውን ፓርቲ/ መንግሥትን የማይተቹ ሆነው ሲገኙ ወይም የመንግስት ትችት ያለባቸው ሆነው ሲገኙ ሃሳቦቹን ቆራርጦ የዘገባ ሽፋን የሚሰጥ መሆኑን ኢዜማ በቃለ መጠይቅ ወቅት የገለፀ መሆኑ፣-
- ኮርፖሬሽኑ ከተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚመጡ የዘገባ ጥቆማዎች በኢዲቶሪያል ስብሰባ ወቅት አብዛኛውን ጊዜ እንዲሰሩ የአየር ሰዓት እንዲያገኙ የማይፈቀዱ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

110. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የኮርፖሬሽኑ የስራ ሃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ በዋናነት የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚስተናገዱት በኤዲቶሪያል ፖሊሲው አማካኝነት ሲሆን በምርጫ ወቅት የምርጫ ዴስክ በማቋቋም ጭምር ለሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ከብሄራዊ የምርጫ ቦርድ በሚደለደለው የአየር ሰዓት አማካኝነት ፍትሀዊ አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን በአጠቃላይ ኮርፖሬሽኑ የምርጫ ህጉን መሰረት ተከትሎ እንደሚሰራ፣ ምንም እንኳን አብዛኛዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች የህዝብ ድምፅ አግኝተው በፌዴራል ወይም በክልል ም/ቤቶች መቀመጫ ባይኖራቸውም የዲሞክራሲ ስርአቱን ለመገንባት ድርሻ እንዳላቸው በማመን ኢቢሲ ተመጣጣኝ የሆነ የአየር ሰአት ለመስጠት ጥረት እንደተደረገ ገልፀዋል፡፡

111. የኮርፖሬሽኑ የበላይ የስራ ሃላፊዎች በመውጫ ስብሰባና በረቂቅ የሪፖርት መልስ ወቅት እንደገለፁት የተፎካካሪ ፓርቲዎች መግለጫዎች በኢዲቲሪያል ኮንፈረስ ታይተው ለዘገባ የሚመጥን መሆኑ እስከተወሰነበት ድረስ የሚሰራጭ መሆኑ፤ ነገር ግን መግለጫው ሌላ ፓርቲን የሚወቅስ ከሆነ ሚዛናዊነቱን ለማስጠበቅ የሌላኛውን ወገን አስተያት ሳይጠየቅ አየር ላይ ማዋል ኤዲቶሪያል ፖሊሲው ስለሚከለክል ሚዛናዊ ያልሆነ መግለጫ ለአየር እንደማይበቃ የገለፁ መሆኑ፡ እንዲሁም በማንኛውም አካል ለአየር እንዲበቁ የሚላኩ መግለጫዎች ህዝብን ከህዝብ የሚያጋጩ ግጭትና ጦርነት የሚቀሰቅሱ ከሆኑ ኮርፖሬሽ ዉግንናው ለህዝብ እንደመሆኑ ህዝቡን ከጥፋት ለመከላከልና መጠበቅ ሃላፊነት ያለበት በመሆኑ በኤዲቶሪያል ፖሊሲውም እንደዚህ አይነት ህዝብን ከህዝን የሚያጋጩ ፤ አመፅና ጦርነት የሚቀሰቅሱ መግለጫዎች እንዳይሰራጩ ስለሚከለክል ሳይሰራጩ እንደሚቀሩ ገልፀዋል ፡፡

112. የኮርፖሬሽኑ የበላይ የስራ ሃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በመገናኛ ብዙሀን አዋጅ ቁጥር 1238/2021 አንቀፅ 56/1ረ እና የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ኢዲቶሪያል ፖሊሲ ገፅ 30 እንደተገለፀው በአገሪቱ ሕገ መንግሥትና የምርጫ ሕግ መሠረት የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ወይም ድርጅቶችን በፍትሃዊነት የሚያገለገልበት የአሰራር ስርዓት መዘርጋት እንዳለበት የሚገለፅ ስለሆነ ፤ ኮርፖሬሽኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚስተናግደው በምርጫ ወቅት ብቻ መሆን እንደሌለበት እና ፓርቲዎች ሃሳባቸውን በስፋት የሚገልፁበት መድረኮች በስፋት መሰራት ስለሚገባ፤ በአሁኑ ወቅት የሚተላለፉ ፕሮግራሞች የፖለቲካ ፓርቲዎችን ሽፋን ለመስጠት የሚሰራው ስራ በቂ ባለመሆኑ የተሰጠው ምላሽ ለመቀበል ያዳግተናል፡፡

113. በመሆኑም ኮርፖሬሽኑ በሚያስተላልፋቸው ዘገባዎችና ፕሮግራሞች የሁሉንም የፖለቲካ ፓርቲዎችን ወይም ድርጅቶችን ያካተት ባለመሆኑ በህዝቡ ዘንድ ኮርፖሬሽኑን የመንግስትን ብቻ መልእክት ማስተላለፊያ እንደሆነ እንዲመለከቱት ያደርጋል፡፡

## ኮርፖሬሽኑ የሰብአዊ መብቶች መከበራቸውን አጉልቶ የሚያሳይ የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ

114. ኮርፖሬሽኑ በሚያቀርባቸው ዜናዎችም ሆነ ፕሮግራሞች የሰብአዊ መብቶች መከበራቸውን አጉልቶ የሚያሳይ የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል ፡፡

115. የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ኤዲቶሪያል ፖሊሲ ገፅ 63 እና የመገናኛ ብዙሀን አዋጅ ቁጥር 1238/2021 አንቀፅ 56/1ሰ እንደተገለፀው ኮርፖሬሽኑ በሚያቀርባቸው

ዜናዎችም ሆነ ፕሮግራሞች የሰብአዊ መብቶች መከበራቸውን አጉልቶ የሚያሳይ የአሰራር ስርዓት እንደሚዘረጋ ይገልፃል ፡፡

116. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች እና ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ መጠይቅ ኮርፖሬሽኑ በሚያቀርባቸው ዜናዎችም ሆነ ፕሮግራሞች የሰብአዊ መብቶች መከበራቸውን አጉልቶ የሚያሳይ ስራዎች በተገቢው መንገድ የተሰራ አለመሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ለማሳያ ያህል፤

- ኮርፖሬሽኑ እንደማንኛውም ተቋም የሰብዓዊ መብቶች የሚያስተናግድ ሲሆን ነገር ግን ለሰብዓዊ መብቶች ዘገባ ተብሎ የራሱ የሆነ ፎርማት/ፕሮግራም/ የሌለው መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከቀረበ በቃለ መጠይቅ የተገኘ መሆኑ፣
- አብዛኛውን ጊዜ በሰብዓዊ መብቶች በኩል የሚወጡ መግለጫዎች ግጭት ቀስቃሽ ናቸው በሚል ምክንያት በኮርፖሬሽኑ በኩል የዘገባ ሽፋን የማይሰጥ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከቀረበ በቃለ መጠይቅ የተገኘ መሆኑ፣
- የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ከነሀሴ 11/2020 እሰከ ታህሳስ 25/2023 ከ178 በላይ በርካታ መግለጫዎችን ያወጣ ሲሆን፣ በኮርፖሬሽኑ በኩል መግለጫዎችን ለህዝቡ እያደረሰ አለመሆኑ፤
- ኮርፖሬሽኑ ሰብአዊ መብቶች ጉዳዮችን በተመለከተ ከ2013-2015 ዓ.ም ድረስ ከ17 በማይበልጡ ጉዳዮች ብቻ የዘገባ ሽፋን የሰጠ መሆኑ መገለፁ፤
- የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን የሚያወጣቸውን በርካታ መግለጫዎች እና መሰል ሪፖርቶች ኢ.ቢ.ሲን ጨምሮ ለበርካታ የሚዲያ ተቋማት በኢ.ሜል እንዲሁም በተቋሙ ሚዲያ እና በማህበራዊ ሚዲያ ይፋ የሚደረግ መሆኑ እና ከዚህ ውስጥ በኮርፖሬሽኑ የአካል ጉዳተኞችና የአረጋዊያን ሪፖርቶች ሽፋን ያገኙ ቢሆንም ከ20-30% የሚሆኑት ብቻ ሽፋን ያገኙ መሆኑን ለኮሚሽኑ ከቀረበው ቃለ መጠይቅ የገለፁ መሆኑ፤
- የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ መግለጫዎች በሚያወጣበት ጊዜ በአካል በኢ.ሜል በፋክስ ለኮርፖሬሽኑ የሚላክ ቢሆንም የዘገባ ሽፋን የማይሰጥ መሆኑ ለጉባኤው ከቀረበው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል ፡፡

117. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የኮርፖሬሽኑ የስራ ሃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ኮርፖሬሽኑ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን የሚልከውን መግለጫ ብቻ ሳይሆን

ኮርፖሬሽኑ ራሱ አቅዶ በተለያዩ ፕራግሮሞች /ዳጉ/ ጭምር የኮሚሽኑ ዋና ኮሚሽነር ጭምር በማስገባት ሲሰራ እንደቆየና  ከዚያ ውጪ በሰብአዊ መብት ኮሚሽን የሚሰጥ መግለጫ እንደማንኛውም ተቋም በኤዲቶሪያል አሰራር ታይቶ የሚወሰን መሆኑን፣ እንዲሁም ኮርፖሬሽኑ ከ2021- 2023 ለሰብአዊ መብት ኮሚሽን የተሰጠው የዘገባ ሽፋን ከ17 በላይ  መሆኑን ገልፀዋል፡፡

118. የኮርፖሬሽኑ የበላይ የስራ ሃላፊዎች በመውጫ ስብሰባና በረቂቅ የሪፖርት መልስ ወቅት እንደገለፁት የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን  የሚያጣቸው ሪፖርቶች እገሌ የተባለ ብሄር እገሌን ብሄር አጥቅቶ ይህንን  ያህል ቁጥር ያለው ብሄር ተወላጆችን  ገደለ የሚል አይነት ዘገባ ውጤታቸው ህዝብን ከህዝብ የሚያጋጭ እና በሀገር ላይ ተጨማሪ ቀውስ ሊያስከትል ስለሚችል እና የኢዲቶሪያል ፖሊሲው ስለሚከለክል እንደህ አይነት መግለጫዎች ለአየር የሚበቁበት ሁኔታ አለመኖሩን ገለፀዋል፡፡ እንዲሁም የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ለመግለጫው ምንጭነት የሚጠቀማቸው መረጃዎች ላይ ለምሳሌ በስልክ ወይም በፌስቡክ እንዳረጋገጥነው ተብሎ የሚሰጥ መግለጫ ክፍተት ስላለባቸው በኤዲቶሪያል ፖሊሲው እንዲህ አይነት መግለጫ የምንጭ አጠቃቀም ውድቅ ሰለሚያደርግ መግለጫው ላይስተናገድ  የሚችልበት ሁኔታ  የሚኖር መሆኑን ገለፀዋል፡፡

119. የኮርፖሬሽኑ የበላይ የስራ ሃላፊዎች  ይህን ይበሉ እንጂ  በኮርፖሬሽኑ ማቋቋሚያ  አዋጅ ላይ ኮርፖሬሽኑ የሰብአዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን መከበር ላይ ትኩረት አድርጎ ይሰራል የሚል በመሆኑ ከኢትዮጵያ  ሰብአዊ መብት ኮሚሽን የሚቀርቡ መግለጫዎች በአብዛኛው ግጭት ለመቀስቀስ ነው ለማለት የማይቻል መሆኑ፤ በኦዲቱም በኩል ግጭት ቀስቃሽ ዘገባ እንዲቀርብ ሳይሆን፤ ከሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ጋር በቅርበት ለመስራት የሚያስችል መግባቢያ ሰነድ በመፈራረም ሆነ በሚመጡ ዘገባዎች ላይ ተሳትፎና ትብብር በማድረግ ትክክለኛና ሚዛናዊ ፕሮግራሞችን ለመስራት መቻል ያለበት በመሆኑ እና ከዚህ አንፃር በኮርፖሬሽኑ የተሰራ በቂ ስራዎች ባለመቅረባቸው የሰጡት ምላሽ ለመቀበል ያዳግተናል፡፡

120. በመሆኑም ኮርፖሬሽኑ ሀገሪቱ የሚከሰቱ የሰብአዊ መብቶች መጣስን የሚያመልከቱ በተለያዩ ድርጅቶች የሚወጡ መግለጫዎችን ሚዛናዊነታቸውን ጠብቆ ትኩረት ሰጥቶ የዘገባ ሽፋን ባለመስጠቱ  በህዝቡ ዘንድ ታማኝነቱን የሚያሳጣው ይሆናል ፡፡

### ኮርፖሬሽኑ ተቃራኒ ሃሳቦች የሚስተናገዱበት የክርክር ፕሮግራም የሚያዘጋጅ መሆኑን በተመለከተ

121. ኮርፖሬሽኑ ተቃራኒ ሃሳቦች የሚስተናገዱበትና ሃሳባቸውን የሚገልፁበት የክርክር ፕሮግራም የሚኖርበትን የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

122. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ኮርፖሬሽኑ ተቃራኒ ሃሳቦች የሚስተናገዱበትና ሃሳባቸውን የሚገልፁበት የክርክር ፕሮግራሞች በበቂ ሁኔታ የማይሰራ መሆኑን መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለማሳያ ያህል

- ኮርፖሬሽኑ ተቃራኒ ሃሳቦች የሚስተናገዱበትና ሃሳባቸውን የሚገልፁበት የክርክር ፕሮግራም ከምርጫ ክርክር ፕሮግራም ውጪ የተሳተፈበት ሁኔታ የሌለ መሆኑንና ኮርፖሬሽኑም አዘጋጅቶ የማያውቅ መሆኑ በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው የታዩ አምስት የተፎካካሪ ፓርቲዎች የገለፁ መሆኑን፤
- ከምርጫ 2013 ዓ.ም ወዲህ ባሉ ጊዜያት የሃሳብ ልዩነት ያላቸው ጉዳዮች ላይ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቀርበው እንዲሞግቱ በኮርፖሬሽኑ ይህ ነው የሚባል በቂ እድል የሰጠ አለመሆኑ ኢዜማ በቃለ መጠይቅ ወቅት የገለፀ መሆኑን፤
- በ2014 ዓ.ም የኮርፖሬሽኑ ፍኖተ ካርታ ላይ እንደተገለፀው ኮርፖሬሽኑ ተቃራኒ ሃሳቦች የሚስተናገዱበትና ሃሳባቸውን የሚገልፁበት የክርክር ፕሮግራም ያልተዘጋጀ ስለመሆኑ የገመገሙ መሆኑ፣
- በሀገሪቱ የሚንቀሳቀሱ ተፎካካሪ ፓርቲዎችም ሆነ ከገዢው ፓርቲ የተለየ አተያይ ወይም አመለካከት ያላቸው ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች በበቂ ሁኔታ የማይስተናገዱ መሆኑን በኮርፖሬሽኑ የ2013-2017 ዓ.ም ስትራቴጂካዊ ዕቅድ ላይ እንደ ችግር የተገለፀ መሆኑ፣
- የኮርፖሬሽኑ ትኩረት ሕዝቡ የሚያስፈልገው ላይ ብቻ ስለሆነና የሕዝቡን ፍላጎት የዘነጋ በመሆኑ ጣቢያዎቹ ታዳሚ እንዳይኖራቸው ያደረገ መሆኑን በ2014 ዓ.ም በተዘጋጀው የኮርፖሬሽኑ ፍኖተ ካርታ ላይ የተገለፀ መሆኑ፣
- በሰኔ 2015ዓ.ም የኢቢሲ ተቋማዊ ሪፎርም የማፅናት ምዕራፍ ሰነድ ላይ እንደተገለፀው ፡-
    - ለመንግስትና ህዝብ ጠቃሚ የሚሆኑ ለፖሊሲ አውጪዎች ግብአት ሊሆኑ የሚችሉ የተለየ ሃሳብ እና እይታ ያላቸው አካላትን በአንድ በኩል በተመሳሳይ ፓኬጅ ውስጥ የማካተት ችግር ያለበት መሆኑ፣ በተፎካካሪ

ፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጠው ጊዜ አናሳ መሆን እንዲሁም ከመንግስት የተለየ ሃሳብ ያላቸውን የተለያዩ ሲቪል ማህበራት እና የሙያ ማህበራትን ሚዲያው ተገቢ ትኩረት  የማይሰጥ መሆኑ፣

- ሚዲያው ህዝቡ በሚፈልገው ደረጃ ሃሳብን በነፃነት እየገለፀበት ነው ማለት የማይቻል መሆኑ እንዲሁም በህዝብ ፍላጎት የተመሰረተ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ አብጠርጥረው የሚያወጡ የልብ ትርታውን የሚያዳምጡ መረጃዎች በአግባቡ እየተሰሩ አለመሆኑ፣
-  ኢቢሲ ብዝሃ ሃሳቦችን ለማንጸባረቅ ልዩ ልዩ ሃሳቦችን ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ማስተናደግ ዓላማው አድርጎ የተቋቋመ የህዝብ ሚዲያ ቢሆንም የኢቢሲ ኤዲቶሪያልም የህዝብ ድምፅ ነኝ ቢልም በተግባር ሲፈተሽ ግን ኢቢሲ የሃሳብ ብዝሃነትን የሚያስተናግድ የህዝብ ድምፅ መሆን ያልቻለ መሆኑ መገለፁን ለማወቅ ተችሏል፡፡

123. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የኮርፖሬሽኑ የስራ ሃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ  በተለይ የሪፎርም ፍኖተ ካርታ አዘጋጅቶ ችግሩን ለይቶ ስራ ከገባ በኋላ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የፖለቲካ ፓርቲዎችን እና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችን እየጋበዘ የሚወያይበት የራሱ የፕሮግራም ፎርማት በኢቲቪ ዜና በኤፍ ኤም አዲስ 97.1 በኢትዮጵያ ሬዲዮ በቋንቋዎች ቻናሎች በስፋት ያለው  መሆኑን  ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም በ2015 ዓ.ም  አራት በሚሆኑ  ይዘቶች ላይ  የፖለቲካ ፓርቲዎች የተሳተፉበት ውይይት የተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

124.  የኮርፖሬሽኑ የበላይ የስራ ሃላፊዎች በመውጫ ስብሰባና በረቂቅ የሪፖርት መልስ ወቅት እንደገለፁት በ2014ዓ.ም በሪፎርሙ ፍኖተ ካርታ ከለያቸው ችግሮች አንዱ ሲሆን በኢቲቪ ዜና ከዜና በሻገር፤ ቡናና ሻይ እና ዳጉ የሚባሉ ፕሮግራሞች ፎርማታቸው ጭምር የሀሳብ ብዝሃነትን የሚያስተናግድ ተደርጎ የተዘጋጀ መሆኑ፤ ነገር ግን ከሀገሪቱ ስፋትና ከፖለቲካ እንቅስቃሴ አንፃር እነዚህ ፕሮግራሞች በቂ  አለመሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

125.  ኮርፖሬሽኑ ተቃራኒ ሃሳቦች የሚስተናገዱበትና ሃሳባቸውን የሚገልፁበት የክርክር ፕሮግራም እና ውይይት በቂ ባለመሆኑ ኮርፖሬሽኑን  ህዝቡ  የተለየ ሃሳብ የማይስተናገድበትና የመንግስት ድምፅ ብቻ የሚተላለፍበት ሚዲያ ነው ብሎ እንዲያምን ያደረገዋል፡፡ በተጨማሪም ለመንግስትና ለህዝብ የሚጠቅሙ ሀሳቦች እንዳይወጡ፣ እንዳይዳብሩ፣ ተሰሚነታቸው እንዲቀንስ እና ችግሮችን ለመቅረፍ እንዳይውሉ ያደርጋል፡፡

## ኮርፖሬሽኑ በሚያስተላልፋቸው የዜና ዘገባዎች የስርጭት ጥራታችውና ተደራሽነት በተመለከተ

126. ኮርፖሬሽኑ በሚያስተላልፋቸው የዜና ዘገባዎች የስርጭት ጥራታቸው በጠበቀ መልኩ ተደራሽነት ሊኖረው ይገባል፡፡

127. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች በኮርፖሬሽኑ በሚያስተላልፋቸው የዜና ዘገባዎች የስርጭት ጥራታቸው በጠበቀና ተደራሽነት ባለው መልኩ ስለመሆኑ ለማውቅ ተችሏል፡፡ ለማሳያ ያህል ፡-

- የኮርፖሬሽኑ የሬዲዮ ማሰራጫ ኤፍ ኤም ጣቢያዎች ካሉት 33ቱም ከተማ አካባቢ በመሆኑ ለገጠሩ ነዋሪዎች የሬዲዮ ስርጭት ተደራሽ አለመሆኑ፣
- ኮርፖሬሽኑ የሬዲዮ ስርጭትን በተመለከተ በ2013ዓ.ም ባጠናው ጥናት መሰረት አብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች የኢትዮጵያ ሬዲዮ ስርጭት የማይሰማ መሆኑ፤
- ኮርፖሬሽኑ ሬዲዮ ስርጭት ጥራትን በተመለከተ በ2013ዓ.ም በራሱ ባለሙያዎች የዳሰሳ ጥናት ባስጠናው መሰረት በተለዩ ክፍተቶች (የስርጭት ጥራት) ማነስና ተደራሽነት ላይ ያሉ ችግሮች የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤ እንዲሁም በ2013ዓ.ም ላይ የነበሩ የሬዲዮ ስርጭት ችግሮች እስከ ህዳር 2016 ዓ.ም ሳይፈቱ አሁንም ድረስ ችግሮቹ ያሉ መሆኑ፤ **ዝርዝሩ በአባሪ 4 ተያይዟል፡፡**
- በ2015 ዓ.ም የሬዲዮ ማሰራጫ ጣቢያዎችን ለማሻሻል ከቀረበው ፕሮፖዛል ለማወቅ እንደተቻለው ኮርፖሬሽኑ የሬዲዮ ስርጭትን ተደራሽ ለማድረግ ካሉት 43 የሬዲዮ ማሰራጫ ጣቢያዎች በተጨማሪ 50 የኤፍ ኤም የማሰራጫ ጣቢያዎች የሚያስፈልጉት መሆኑ መገለፁ፣
- በ2015 ዓ.ም የሬዲዮ ማሰራጫ ጣቢያዎችን ለማሻሻል ከቀረበው ፕሮፖዛል ለማወቅ እንደተቻለው ኮርፖሬሽኑ ካሉት 43 የሬዲዮ ማሰራጫ ጣቢያዎች እና የኤፍኤም ትራንስሚተሮች የተወሰኑት የሬዲዮ ማሰራጫ ጣቢያዎች እና የኤፍኤም ትራንስሚተሮች የሚያሰራጩት ካላቸው አቅም በታች መሆናቸው፣
- ኮርፖሬሽኑ 50 የኤፍ ኤም የማሰራጫ ጣቢያዎች ለመገንባት በፕሮፖዛል ደረጃ ብር 689,412,094.47 (ስድስት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ሚሊዮን አራት መቶ አሰራ ሁለት ሺ ዘጠና አራት ብር ከ47/100 ሳንቲም) የሚያስፈልግ መሆኑ፣

እንዲሁም ለማሰራጫ ጣቢያ ግንባታ የተፈለገው በጀት በመንግስት ድጋፍ በኩል ይሁን በኮርፖሬሽኑ ገቢ የተፈቀደ በጀት አለመኖሩ፣

- በተደጋጋሚ ከአድማጭ ተመልካች ግብረ መልስ ሪፖርት ለማወቅ እንደተቻለው ኮርፖሬሽኑ የሬዴዮ ስርጭት ጥራት ችግርና ተደራሽነት ላይ በተደጋጋሚ የህዝብ ቅሬታዎች የሚነሱበት ሲሆን ነገር ግን ኮርፖሬሽኑ ችግርን ለመፍታት የሄደበት ሁኔታ የሌለ መሆኑ፣
- በኮርፖሬሽኑ ከሚቀርቡ የአድማጭ ተመልካች አስተያየቶች መካከል በብዛት የስርጭት መቋረጥና የስርጭት ጥራት ማነስ የሚገልፅ መሆኑ፣
- በኮርፖሬሽኑ የ2013-2017 ዓ.ም ስትራቴጂካዊ ዕቅድ ላይ እንደተገለፀው የመካከለኛ ሞገድ ሬዴዮ ማሰራጫ ጣቢያዎች ለረዥም አመታት ያገለገሉ፣ ከቴክኖሎጂ እድገት አንጻር ኋላ ቀርና የመለዋወጫ ዕቃ እጥረት ያለባቸው መሆኑ እንዲሁም የስርጭት ጥራት ደረጃቸውም የወረዱ መሆናቸው መገለፁ፣
- በኮርፖሬሽኑ የ2013-2017ዓ.ም ስትራቴጂካዊ ዕቅድ ላይ እንደተገለፀው በኤፍ.ኤም. ትራንስሚተሮች ስርጭት ያልተሸፈኑ አካባቢዎች በመኖራቸው እና የስርጭት ችግር ያለ ቢሆንም ይህን ችግር ለመቅረፍ ስርጭቱን በቀላል መቀበያ ሊደመጥ እንዲችል ለማድረግ በስትራቴጂያዊ ዕቅድ ዘመኑ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም ያሉትን ከማስቀጠል ውጪ ሌላ የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣
- በሀገሪቱ ባሉት የትራንስሚተር ጣቢያዎች የመብራት መቋረጥን ተከትሎ ስርጭቱን በጀነሬተር ለመሸፈን ቢሞከርም ጀነሬተሮቹ ረዘም ላለ አመታት ያገለገሉ በመሆናቸው በአሁኑ ሰዓት ከፍተኛ የነዳጅ ፍጆታ ስለሚጠቀሙ ጥዋትና ማታ ለአንድ ሰዓት ብቻ እንዲሰሩ የሚደረግ መሆኑ፣
- በአብዛኛው የሬዲዮ የማሰራጫ መሳሪያ መጠባበቂያ የሌላቸው መሆኑ በተጨማሪም ኮርፖሬሽኑ ምንም አይነት የሬዲዮ ማሰራጫ ጣቢያ መለዋወጫ ከአስር አመት በላይ ያልተገዛ መሆኑ፣ ለማወቅ ተችሏል፡፡ (**የኢትዮጵያ ሬዲዩ የማይሰማባቸው አካባቢዎች ዝርዝሩ እና የማሰራጫ ጣቢያዎች አቅም በተመለከተ በአባሪ 5 እና 9 ተያይዟል**)

128. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የኮርፖሬሽኑ የስራ ሃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ኮርፖሬሽኑ 9 የመካከለኛ ሞገድ ሬዲዮ ማሰራጫ የኢትዮጲያ ሬዲዮን

በተለይ የገጠሩን ህብረተሰብ ክፍል ታሳቢ አድርጎ የሚያሰራጭ ሲሆን 34 የኤፍኤም ማሰራጫ ጣቢያዎች 17 ኤፍ ኤም አዲስ 97.1 ፕሮግራሞችን የሚያሰራጩ እንዲሁም 17 የኢትዮጲያ ሬዲዮን የሚያሰራጩ የተለያዩ አቅም ያላቸው ማሰራጫዎች ባለቤት እንደሆነ፣ ነገር ግን በበጀት እጥረት በውጪ ምንዛሪ ችግር እና በመለዋወጫ ዕቃ እጥረት አብዛኛዎቹ መካከለኛ ሞገድ ሬዲዮ ማሰራጫ ጣቢያዎች በከፊል አቅም የሚሰሩ በመሆኑ የስርጭት የጥራት ችግር ያለ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም በየአካባቢው የመብራት መቆራረጥ ምክንያት የስርጭት መቆራረጥ እንደሚያጋጥም፣ የ50 ዲጂታል ሬዲዮ ፕሮጀክት በ3 ዙር የሚከናወን ፕሮጀክት ሲሆን በ2016 ዓ.ም ለመጀመሪያው ዙር /የ20 ማሰራጫ ጣቢያዎች ግንባታ / የፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከገንዘብ ሚኒስቴር መፈቀድ ያለበት በጀት ባለመፈቀዱ ትግበራው ሊጀመር እንዳልቻለ፤ ይህም ሆኖ በሬዲዮ ስርጭት እና የገጠሩን ማህበረሰብ ክፍል በመድረስ በኩል በሀገሪቱ ውስጥ ካሉ ሚዲያዎች ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ የሆነ ሽፋን ያለው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

129. የኮርፖሬሽኑ የበላይ የስራ ሃላፊዎች በመውጫ ስብሰባና በረቂቅ የሪፖርት መልስ ወቅት እንደገለፁት የሬዲዮ ስርጭትን ተደራሽት በዘላቂነት ለመፍታት በእቅድ የተያዘ የዲጅታል የሬዲዮ ፕሮጀክት ያለ ሲሆን ለፕሮክቱ ማስፈፀሚያ የሚሆን በጀት ተጠይቆ ከመንግስት በጀቱ ባለፈቀዱ ምክንያት እስካሁን ስራው አለመጀመሩን ገለፀዋል፡፡

130. በመሆኑም ኮርፖሬሽኑ የሚያስተላልፋቸው ዜናዎችና ፕሮግራሞች በህዝቡ በተለይም በገጠሩ አካባቢዎች የሚኖር ህብረተሰብ ዘንድ እንዳይደመጡ ያደርጋል፡፡ እንዲሁም ማህበረሰቡ በሀገሪቱ ያለውን ማህበራዊ ፤ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ግንዛቤ እንዳይኖራቸው ያደርጋል፡፡

**ኮርፖሬሽኑ የዜና ዘገባ የሁነትና የፕሮጀክት በሚያሳይ መልኩ መሆኑን በተመለከተ**

131. ኮርፖሬሽኑ በሚሰራቸው የዜና ዘገባ እቅድ የሁነትና የፕሮጀክት የዜና ብዛት በሚያሳይ መልኩ ሊቀመጥ ይገባል፡፡

132. ይሁን እንጂ ኮርፖሬሽኑ በሚሰራቸው የዜና ዘገባ እቅዶች 30% የሁነት እና 70% የፕሮጀክት የሚለውን መርህ እየተከተለ አለመሆኑን ከ2015 ዓ.ም እቅድ አፈፃፀም ለማወቅ ተችሏል፡፡

133. በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች የሚከተሉት ተገኝተዋል፡-

- የኮርፖሬሽኑ ከፍተኛ አመራር በተለይም የይዘት ስራዎች ከሁነትና ከጥድፊያ ስራ ወጥተው በዕቅድ የሚመሩና ጥልቀት ያላቸው ሆነው እንዲሰሩ የማድረግ ክፍተት

እንዳለበት በኮርፖሬሽኑ የ2013-2017 ዓ.ም ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ላይ የተገለፀ መሆኑ፣

- የኮርፖሬሽኑ አብዛኛዎቹ ዜናዎች በመንግስት መደበኛ ስራ ላይ የሚያተኩሩ ስለሆኑ የአየር ሰዓቱ በነሱ ስለሚያዝ ህዝባዊ ጉዳዮችን የሚዳስሱ ይዘቶች በጣም አነስተኛ መሆናቸውን በሰኔ 2015 ዓ.ም የኢቢሲ ተቋማዊ ሪፎርም የማፅናት ምዕራፍ ሰነድ ላይ የተገለፀ መሆኑ፣
- በመጋቢት 27/2015 ዓ.ም በቦርዱ ቃለ ጉባኤ እንደተመለከተው የፕሮጀክት ዜና ሽፋን 60% መድረሱ የተገለፀ ቢሆንም፤ በኮርፖሬሽኑ የ2015 ዓ.ም በጀት ዓመት የ9ወራት አፈጻጸም ሪፖርት የተሰሩ ዘገባዎች በፕሮጀክት 2327፣ በሁነት 11971 መሆኑ፤
- ኮርፖሬሽኑ በ2013 ዓ.ም እና የ2014 ዓ.ም የሰራቸውን ዜናዎች የሁነትና የፕሮጀክት ዜናዎች በማለት ለይቶ በእቅድ አፈፃፀሙ ላይ በቁጥር ደረጃ ያላስቀመጠ መሆኑ፣ ለማወቅ ተችሏል፡፡

134. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የኮርፖሬሽኑ የስራ ሃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ኮርፖሬሽኑ ራሱ በዘገባዎች የሁነት ዜናዎች መብዛታቸውን ገምግሞ ወደ ፕሮጀክት ዜና ማተኮር እንዳለበት በመርህ ደረጃ የተቀመጠው በ2015 ዓ.ም ሲሆን በተለይ ከሐምሌ 1 ቀን 2015 ጀምሮ ይህንን የፐርሰንቴጅ ምጣኔ ለማሳካት እየሰራ እንደሚገኝ፣ በተቋማዊ ሪፎርሙ ቅድሚያ የተሰጠው ለአማርኛ ዜናና ወቅታዊ ጉዳዮች ስለነበር የቋንቋዎች ዜና በሚፈልገው ደረጃ ፕሮጀክት ላይ ያላተኮረ መሆኑን፣ በ2016 ዓ.ም እቅድ ውስጥ ግን ሁሉም ቻናሎች ፕሮጀክት ዜና ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ አቅጣጫ የተሰጠ መሆኑን፣ በሌላ ለኩል የፕሮጀክት ዜናዎችን በእቅዱ መሰረት ለማከናወን በሀገሪቱ ያለው አጠቃላይ የፀጥታ ሁኔታ የማይፈቅድ መሆኑ መታየት ይኖርበታል በማለት ገልፀዋል ፡፡

135. በመሆኑም ኮርፖሬሽኑ ትኩረት አድርጎ የሚሰራቸው የዜና ዘገባዎች በብዛት የሁነት ወይም የመንግስት ስብሰባዎችና በዓላቶች ላይ በመሆኑ በፕሮጀከት ወይም በእቅድ የሚሰራቸው ዜናዎች ዝቅተኛ እዲሆኑ ከማድረጉ ባሻገር የህዝቡን ችግሮች ነቅሶ በማውጣትና መንግስትና ባለድርሻ አካላት መፍትሄ እንዲፈልግላቸው ከማድረግ አንፃር ክፍተት እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡

## IV. የኮርፖሬሽኑን የዜና አገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል የሚችሉ የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፤

### ኮርፖሬሽኑ በሚያቀርባቸው ዘገባዎች እና ፕሮግራሞች ላይ የዳሰሳ ጥናት ማከናወኑን በተመለከተ

136. ኮርፖሬሽኑ በሚያቀርባቸው ዘገባዎች እና ፕሮግራሞች ላይ የህዝቡን ስሜት ለማወቅ በናሙና ላይ የተመሰረተ የዳሰሳ ጥናት ሊያከናውን ይገባል፡፡

137. በኮርፖሬሽኑ የኤዲቶሪያል ፖሊሲ ገፅ 106 እንደተገለፀው ኮርፖሬሽኑ በሚያቀርባቸው ዘገባዎች እና ፕሮግራሞች ላይ የህዝቡን ስሜት ለማወቅ በናሙና ላይ የተመሰረተ የዳሰሳ ጥናት እንደሚያከናውን እንዲሁም በኢዲቶሪያል ፖሊሲ ገፅ 107 እንደተገለፀው ኮርፖሬሽኑ ገለልተኛና ሙያዊ ብቃት ባላቸው የውጭ አካላት ቢያንስ በሁለት አመት አንድ ጊዜ የአድማጭ ተመልካች ጥናት እንደሚያከናውን ይገልፃል ፡፡

138. ይሁን እንጂ ኮርፖሬሽኑ በሚያቀርባቸው ዘገባዎች እና ፕሮግራሞች ላይ የህዝቡን ስሜት ለማወቅ በናሙና ላይ የተመሰረተ ተከታታይነት ያለው የአድማጭ ተመልካች የዳሰሳ ጥናት ከ2012-2016 ዓ.ም ባለው ጊዜ በራስ አቅምም ሆነ ገለልተኛና ሙያዊ ብቃት ባላቸው የውጭ አካላት አንድም ጊዜ አድርጎ የማያውቅ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች እና ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ከቀረበው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

139. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የኮርፖሬሽኑ የስራ ሃላፊዎች ተጠይቀው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ኮርፖሬሽኑ በሪፎርም ስራ ላይ ስለነበረ ከሚዲያ ኮምፕሌክስ ግንባታ ጋር ተያይዞ ከፍተኛ ወጪ ስለወጣ በበጀት እጥረት ምክንያት የአድማጭ ተመልካች ጥናት ያልተደረገ ቢሆንም ከማእከላዊ ስታስቲክስ ባለስልጣን ጋር በጋራ ለመስራት ፕሮፖዛል ቀርቦ ከ 4 ሚሊዮን ብር በላይ እንደተጠየቀ ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም የኮርፖሬሽኑ የጥናት እና ምርምር ዲፓርትመንት ጥናት እንዳካሄደና መረጃው ከነባራዊ ሁኔታ መግለጫው ምላሽ ጋር ተያይዞ ለኦዲት ቡድኑ እንደቀረበ ገልፀዋል፡፡

140. የኮርፖሬሽኑ የበላይ የስራ ሀላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ ከነባራዊ ሁኔታ መግለጫው መልስ ጋር የተያያዘው በኮርፖሬሽኑ የሚተላለፉ ፕሮግራሞች ላይ የአድማጭ ተመልካች ግብረ መልስ እንጂ የዳሰሳ ጥናት አለመሆኑ፣ እንዲሁም ተከናውኗል የተባለው የአድማጭ ተመልካች እርካታ የደሰሳ ጥናት ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ እንደምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

141. በመሆኑም ኮርፖሬሽኑ በሚያስተላልፋቸው ዜናዎችና ፕሮግራሞች የአድማጭ ተመልካቾች የእርካታ ደረጃ በምን ያህል ደረጃ እንደሆነ፣ ተቀባይነቱ እና ፍላጐት እንዲቀጥሉ እና አዲስ እንዲተከሉ የሚፈልጓቸው ወይም የማይፈልጓቸው ፕሮግራሞች በመለየትና ክፍተቶች ለመሙላት እና ለማሻሻል እንዳይችል ያደርጋል፡፡

**ኮርፖሬሽኑ የአድማጭ ተመልካችን ቅሬታዎችን መፍታቱን በተመለከተ**

142. ኮርፖሬሽኑ የአድማጭ ተመልካች ቅሬታዎችን የሚፈታበትና ግብረመልስ የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

143. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ኮርፖሬሽኑ የአድማጭ ተመልካች ግብረመልስ የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፤ እንዲሁም ኮርፖሬሽኑ ለአድማጭ ተመልካቾች ለሚቀርቡ ቅሬታዎች በምን ሁኔታ እና መቼ ግብረ መልስ መስጠት እንዳለበት በግልፅ የተቀመጠ የአሰራር ስርዓት የሌለው መሆኑ ለመረዳት ተችላል፡፡ ለማሳያ

- በኮርፖሬሽኑ ከሚቀርቡ የአድማጭ ተመልካች አስተያየቶች መካከል በብዛት የስርጭት መቋረጥና የስርጭት ጥራት ማነስ መሆኑ፤ይህም በየጊዜው ችግሮቹ እየቀጠሉ በመሆኑ ችግሮቹን ተከታትሎ መፍትሄ ከመስጠትና ችግሮቹ እንዳይከሰቱ ከማድረግ አንፃር ክፍተት ያለበት መሆኑ፤
- በነሀሴ 2013 ዓ.ም፣ በታህሳስ 2014 ዓ.ም፣ በግንቦት 2015 ዓ.ም የአድማጭ ተመልካች የግብረ መልሰ ትንተና ላይ እንደተገለፀው ለኢትዮጵያ ሬዲዮ እና ኤፍ. ኤም 97.1 የስርጭት መቋረጥ፣ የስርጭት መቆራረጥ፣ የድምጽ ጥራት መጓደልና ወጣ ገባ ማለትን በተመለከተ የቀረቡ ቅሬታዎች ያሉ ሲሆን፤ ምንም ዓይነት በአድማጭ ተፈላጊ የሆነ ይዘት/መረጃ በጣቢያው ቢያዘጋጅ ያለ ስርጭት ውጤት አልባ መሆኑን በመገንዘብ ችግሮቹ ያልተፈቱ መሆኑ፤ እንዲሁም መረጃ ከማግኘት አኳያ የኢትዮጵያ ሬዲዮና ኤፍ ኤም 97.1 ብቸኛ አማራጭ ለሆነባቸው አድማጮች ችግሩ ያጋጠማቸውን አካባቢዎችና የስርጭቱን ችግር በመውሰድ በኢቢሲ የቴክኒክ ክፍል ጉዳዩ ትኩረት ተሰጥቶት በማያዳግም ሁኔታና በዘላቂነት የስርጭት ችግር መፈታት እንዳለበት የተገለፀ መሆኑ፤ እንዲሁም የሚቀረቡ ቅሬታዎችን በኮርፖሬሽኑ በኩል እነዚህን ቅሬታዎች እየፈታ አለመሆኑን የሚያሳይ መሆኑ፤

- ለኮርፖሬሽኑ ከአድማጭ ተመልካች የኢትዮጵያ ሬዲዮ የስርጭት መቋረጥና ተደራሽነት ላይ ቅሬታዎች የሚቀርቡ ሲሆን ነገር ግን የቀረቡ ቅሬታዎች ስለመፈታታቸው የሚያሳይ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

144. የኮርፖሬሽኑ የበላይ የስራ ሃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መልስ ላይ እንደገለፁት የአድማጭ ተመልካች አስተያየት በማስተባበሪያው በኩል ከተሰበሰበ በኋላ በዘገባ የሚሸፈነው በዘገባ፣ በፕሮግራም የሚሸፈነው ደግሞ ፕሮግራም እንዲሰራበት ለኤዲቶሪየል ኮንፍረንስ እንዲቀርብ የሚደረግበት ስርአት አለ፡፡ በየእለቱ የሚሰበሰበው ኤዲቶሪያል አንዱ የሚወስነው ከአድማጭ ተመልካች የሚቀርቡ አስተያየቶች እና ግብረ መልሶች መሆኑን ገልፀዋል፡፡

145. የኮርፖሬሽኑ የበላይ ኃላፊዎች ይህን ቢሉም ኮርፖሬሽኑ ከአድማጭ ተመልካች የሚቀርቡ አስተያየቶች የሚቀበልበት እና ግብረ መልሶች የሚሰጥበት የአሰራር ስርአት ያለው ሲሆን፣ ነገር ግን ከአድማጭ ተመልካች የሚቀርቡ ቅሬታዎች እንዴት እንደሚፈቱ እና በምን አይነት ስርዓት እንደሚሄዱ የሚገለፅ መረጃ ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

146. በመሆኑም ኮርፖሬሽኑ በህዝቡ የሚነሱ ቅሬታዎችን ተከታተሎ የሚፈታበት ስርዓት ያልዘረጋ በመሆኑ የሚቀርቡ ቅሬታዎች ላይፈቱ የሚችሉበት ሁኔታ መኖሩ፣ በዚህም ምክንያት በኮርፖሬሽኑ የሚያስተላልፋቸው ዜናዎችና ፕሮግራሞች በህዝቡ ዘንድ አድማጭና ተመልካች እንዳይኖራቸው ሊያደርግ ይችላል፡፡

# ክፍል ሶስት

## መደምደሚያ

147. ከላይ በኦዲት ግኝቶቹ ላይ እንደተመለከተው በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የሚሰራቸው የሬዲዮና የቴሌቪዥን የዜናና ወቅታዊ ጉዳዮች አገልግሎት አሰጣጥ አፈፃፀም ውጤታማነት ላይ የታዩት ግኝቶች የሚከተሉት መደምደሚያ ሃሳቦች ላይ ተደርሷል፡-

- የኮርፖሬሽኑ የስራ አመራር ቦርድ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽንን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 1278/2015 የተሰጡትን ዝርዝር ኃላፊነቶች ለመስራት የሚያስችል የሥራ መመሪያ የሌለው እና ኃላፊነቶቹን ለመወጣት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ ታውቋል፡፡
- የኮርፖሬሽኑ ቦርድ አመራር ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ስብሰባውን የማያደርግ መሆኑ፤ እንዲሁም ቦርዱ ኮርፖሬሽኑን ወደ ተሻለ ምዕራፍ ሊያሸጋግሩ የሚችሉ እቅዶችን አቅዶ ከመስራት አንፃርና የተቋሙን ጊዜያዊና ዘላቂ ችግሮችን ለመቅረፍ በሚያስችል መልኩ ወቅቱን የጠበቀ ግንኙነት በማድረግ ረገድ ክፍተት ያለበት መሆኑ ታውቋል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ የአርካይቭ ሀብትን ዲጅታላዝ ለማድረግ በተለይም የድሮ ካሴቶች መገልበጫ ማሽን በሀገር ውስጥ አለመኖር ሲሆን ኮርፖሬሽኑ ይህንን ማሽን በግዢ ወይም በኪራይ ለማግኘት እንዲቻል በጀት እንዲፈቀድ ለገንዘብ ሚኒስቴርና ለፕላን ሚኒስቴር ጥያቄ የቀረበ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ችግሩ ያልተፈታ መሆኑ ተገንዝበናል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ የሚዲያውን ኢንዱስትሪ እና የአገሪቱን የእድገት ሽግግር ከግምት ውስጥ በማስገባት የኤዲቶሪያል ፖሊሲው ወቅታዊ አላደረገም፡፡
- ኮርፖሬሽኑ ኤዲቶሪያል ነፃነት በተጠበቀ እና በሥራውም ሆነ በአስተዳደሩ ከመንግሥትና የመንግሥት ተቋማትን ጨምሮ ከማንኛውም አካል ነፃና ገለልተኛ ሆኖ እየሰራ አለመሆኑ ታውቋል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ በቋንቋዎች ከሚያሰራጫቸው የዜና ይዘቶች 70% በክልል 30% በማዕከል መሆን ሲገባው አብዛኞቹ የማዕከል ዜናዎች ላይ ያተኮሩ በመሆኑ በየክልሎቹ ነባራዊ ሁኔታ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ላይ ክፍተቶች ተገኝተዋል፡፡

- ኮርፖሬሽኑ የፖለቲካ ፓርቲዎችን በፍትሀዊነትና ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማገልገል የሚችል የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣ እንዲሁም ኮርፖሬሽኑ ተቃራኒ ሃሳቦች የሚስተናገዱበትና ሃሳባቸውን የሚገልፁበት የክርክር ፕሮግራም እና ውይይት 2015 ዓ.ም የጀመረ ቢሆንም በቂ እና አካታችነት ላይ ክፍተት ያለው መሆኑ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ በሚያቀርባቸው ዜናዎችም ሆነ ፕሮግራሞች የሰብአዊ መብቶች መከበራቸውን አጉልቶ የሚያሳይ የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣ እንዲሁም በሰብዓዊ መብት ላይ በስፋት ለመስራት ከሰበአዊ መብት ኮሚሽን ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድም ሆነ በሚያቀርቡት ዘገባ/ፕሮግራም ላይ በጋር ለመስራት የሚያስችል መድረክ ያላዘጋጀ መሆኑ ታውቋል ፡፡
- ኮርፖሬሽኑ በሚያስተላልፋቸው የሬዲዮ የዜና ዘገባዎች እና ፕሮግራሞች የስርጭት ጥራታቸው በጠበቀ እና ተደራሽነት ባለው መልኩ አለመሆኑ፣ በኮርፖሬሽኑ የሚተላለፉ የሬዲዮ ስርጭት አብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች የኢትዮጲያ ሬዲዮ ስርጭት የማይሰማ እና ደካማ ስርጭት ያለው መሆኑ፣ እንዲሁም ኮርፖሬሽኑ ካሉት 43 የሬዲዮ ማሰራጫ ጣቢያዎች እና የኤፍኤም ትራንስሚተሮች የተወሰኑት የሬዲዮ ማሰራጫ ጣቢያዎች እና የኤፍኤም ትራንስሚተሮች የሚያሰራጭ ቢሆንም አቅም በታች መሆናቸው፣ የኮርፖሬሽኑ የሬዲዮ ኤፍኤም ማሰራጫ ጣቢያዎች አብዛኛዎቹ ያሉት ከተማ አካባቢ በመሆኑ ለገጠሩ ነዋሪዎች የሬዲዮ ስርጭት ተደራሽ አለመደረጋቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ በሚያቀርባቸው ዘገባዎች እና ፕሮግራሞች ላይ የህዝቡን ስሜት ለማወቅ በናሙና ላይ የተመሰረተ ተከታታይነት ያለው የዳሰሳ ጥናት በራስ አቅምም ሆነ ገለልተኛና ሙያዊ ብቃት ባላቸው የውጭ አካላት ጥናት ያልተደረገ በመሆኑ የአድማጭ ተመልካች እርካታ ምን ላይ እንዳለ የማይታወቅ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ ከአድማጭ ተመልካች የሚቀርቡ አስተያየቶች የሚቀበልበት እና ግብረ መልሶች የሚሰጥበት የአሰራር ስርአት ያለው ሲሆን፣ ነገር ግን ከአድማጭ ተመልካች የሚቀርቡ ቅሬታዎች እንዴት እንደሚፈቱ እና በምን አይነት ስርዓት እንደሚከናወኑ የተቀመጠ ግልፅ የአሰራር ሥርዓት አልተዘረጋም፡፡

# ክፍል አራት
# ማሻሻያ ሀሳቦች

148. በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ክፍተቶችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

- የኮርፖሬሽኑ የስራ አመራር ቦርድ በአዋጁ የተሰጡትን ዝርዝር ተግባራትን ለመወጣትና ስራዎችን ለመስራት የራሱ የሆነ የስራ መመሪያ ሊያወጣ ይገባል፡፡
- የኮርፖሬሽኑ ስራ አመራር ቦርድ የመገናኛ ብዙሃንን በሚመለከት የመንግስት ፖሊሲዎችን እና ህጎችን በኮርፖሬሽኑ ተግባራዊ መሆናቸውን በመከታተል እና በመቆጣጠር ስራውን የሚያረጋገጥበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
- የኮርፖሬሽኑ ስራ አመራር ቦርድ በኮርፖሬሽኑ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ሚዲየሞች የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ያካተተ የሃሳብና የይዘት ብዝሃነት ያላቸው ፕሮግራሞች ተቀርፀው ለህዝብ መቅረባቸውን የሚከታተልበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል ፡፡
- የኮርፖሬሽኑ ስራ አመራር ቦርድ ኮርፖሬሽኑ በሚሰጠው የቴሌቪዥን እና የሬዲዮ አገልግሎቶች ለማህበረሰቡ በሚያደርሳቸው መረጃዎች ህዝቡ ተጠቃሚ መሆኑን የሚገመግምበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል ፡፡
- የኮርፖሬሽኑ ስራ አመራር ቦርድ የተለያዩ አመለካከት ያላቸው በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶችና የህብረተሰብ ክፍሎች ሚዛናዊና ፍትሃዊ የሆነ የሬዴዮና የቴሌቪዥን አገልግሎቶችን በኮርፖሬሽኑ በኩል ማግኘታቸውንና መጠቀማቸውን የሚከታተልበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል ፡፡
- የኮርፖሬሽኑ ስራ አመራር ቦርድ በራዴዮ፣ በቴሌቪዥን ፣ በዲጅታል ሚዲያ እና በሌሎች ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች የሚተላለፉ የፕሮግራም ይዘቶች ወጥነትና ቀጣይነት ባለው መልኩ የሚገመግምበትና ስለሚሻሻልበት ሁኔታ ሃሳብ የሚያቀርብበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል ፡፡
- የኮርፖሬሽኑ ስራ አመራር ቦርድ ከአድማጭ ተመልካቾች በኮርፖሬሽኑ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በአግባቡ ለይቶ እንዲያውቅና የመፍትሂ አቅጣጫ እንዲያስቀምጥ የሚመረምርበትና ተገቢውን ውሳኔ የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል ፡፡

- የኮርፖሬሽኑ ስራ አመራር ቦርድ በኮርፖሬሽኑ የሚተላለፉ ፕሮግራሞች ተደራሽ ያልሆነባቸውና የጥራት ችግር ያለባቸው አካባቢዎች በቀላሉ በማወቅና የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ እንዲችልና በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ተደራሽ መሆናቸውን የሚከታተልበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል ፡፡
- የኮርፖሬሽኑ የስራ አመራር ቦርድ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ሊሰበሰብና የስራ አመራር ቦርዱ ኮርፖሬሽኑን ወደ ተሻለ ምዕራፍ ሊያሸጋግሩ የሚችሉ እቅዶችን አቅዶ በመስራት የተቋሙን ጊዜያዊና ዘላቂ ችግሮችን ለመቅረፍ በሚያስችል መልኩ ወቅቱን የጠበቀ ግንኙነት ሊያደርግ ይገባል ፡፡
- ኮርፖሬሽኑ የአርካይቭ ሀብትን ዲጅታላዝ በማድረግ ለመያዝ ከፍተኛ ችግር የሆነው በተለይም የድሮ ካሴቶች መገልበጫ ማሽን በሀገር ውስጥ አለመኖር መሆኑን የገለፁ ሲሆን፤ ይህንን ማሽን በግዢ ወይም በኪራይ ለማግኘት እንዲቻል ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት እንደ ለገንዘብ ሚኒስቴርና ለፕላን ሚኒስቴር ትኩረት በመስጠት ዲጂታላይዝ በማድረግ የሀገር ሀብት ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ በማስቀመጥ ከትውልድ ትውልድ እንዲተላለፍ እና ለምርምርና ለትምህርት እንዲውል ሊያደርጉ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ የኤዲቶሪያል ፖሊሲውን ተጨባጭ ሁኔታዎችንና ወቅቱ የሚጠይቀውን የሚዲያ ኢንዱስትሪውን ለውጥና ዕድገት በማካተት በየአምስት አመቱ ሊከልስ ይገባል፡፡ እንዲሁም የኤዲቶሪያል ፖሊሲው ተከትሎ በሚወጡ መመሪያዎች ላይ በየጊዜው ክፍተታቸውን እየፈተሹ ደረጃቸውን እንዲጠብቁም ሆነ የአሰራር ውጤታማነት እንዲያስገኙ ሊያድግ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ የኤዲቶሪያል ነፃነት በተጠበቀ እና በሥራውም ሆነ በአስተዳደሩ መንግሥትና የመንግሥት ተቋማትን ጨምሮ ከማንኛውም አካል ነፃና ገለልተኛ ሆኖ ህዝቡ የሚፈልገውን መረጃ ሊያቀርብ ይገባል ፡፡
- ኮርፖሬሽኑ በቋንቋዎች ከሚያሰራጫቸው ስርጭቶች እስከ 70% ሽፋናቸው በክልሎች በሚከናወኑ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸው የተሞክሮ ልምድ ልውውጥ ሊደረግባቸው በሚገቡ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አደርጎ በመስራት ለማህበረሰቡ መረጃ ሊያደርስ ይገባል ፡፡

- ኮርፖሬሽኑ በአገሪቱ ሕገ መንግሥትና የምርጫ ሕግ መሠረት በሀገሪቱ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ወይም ድርጅቶችን በሬዴዮና በቴሌቪዥን ሚዲየሞች በፍትሃዊነት እና ሚዛናዊነትን በጠበቀ መልኩ አገልግሎት የሚሰጥበትና ከምርጫ ዉጭ ባለዉ ጊዜም የፖለቲካ ፓርቲዎች ሃሳባቸዉን መግለጽ የሚችሉበት ሁኔታ ሊያቻችና የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል ፡፡
- ኮርፖሬሽኑ በሚያቀርባቸው ዜናዎችም ሆነ ፕሮግራሞች የሰብአዊ መብቶች መከበራቸውን አጉልቶ የሚያሳይ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ እንዲሁም ከሰበአዊ መብቶች ኮሚሽን ጋር የሰብአዊ መብቶች በተመለከተ በጋራ ለመስራት የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ ሊፈራረም ወይም በጋራ ለመስራት የሚችሉበትን ሁኔታ ሊዘረጋ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ ከተለያዩ የመንግስት መ/ቤቶ፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የሰብአዊ ድርጅቶች የዘገባ ሽፋን ጥቆማ በሚያቀርቡበት ወቅት በኮርፖሬሽ የኢዲቶሪያል ኮንፈረስ ውይይት ጊዜ የዜናን መስፈርት አያሟሉም ብሎ እንዳይቀርቡ በሚያደርግበት ጊዜ ምክንያቱን ለጥቆማ አቅራቢዎች የሚያሳውቅበት ግልፅና ተጠያቂነት ያለው ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ ተቃራኒ ሃሳቦች የሚስተናገዱበትና ሃሳባቸውን የሚገልፁበት የክርክር ፕሮግራም በስፋት ሊያዘጋጅ እና ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ተሳታፊ የሚያደርግበትን የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል ፡፡
- ኮርፖሬሽኑ የሚያስተላልፋቸው ዜናዎችና ፕሮግራሞች በህዝቡ እንዲደመጡና ማህበረሰቡ በሀገሪቱ ያለውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሬዲዮና የቴሌቪዥን የስርጭት ጥራታችው የጠበቀ እና ተደራሽነት ባለው መልኩ ሊያስተላልፍ ይገባል ፡፡
- ሬድዮ ስርጭት በቀላሉ ከቦታ ቦታ ይዞ በመንቀሳቀስ ወቅታዊ መረጃ ከዳር እስከ ዳር በማዳረስ፣ በማስተማር፣ በማዝናናት እንዲሁም መንግስትንና ህዝብን እንደ ድልድይ ሆኖ በማገናኘት አውንታዊ ሚና የሚጫወት ሲሆን፣ እንዲሁም በሀገራችን 80% የገጠር ነዋሪ በመሆኑ መረጃዎችንም በብዛት የሚያገኙት በሬዲዮ በመሆኑ ኮርፖሬሽኑ ሬዲዮ ስርጭት ላይ ትኩረት አድርጎ ሊሰራ ይገባል፡፡

- ኮርፖሬሽኑ ከሚሰራቸው የዜና ዘገባዎች እንዳሉ ሆኖ የፕሮጀክት ዜናዎችን ላይ ትኩረት በማድረግ  የህዝቡን ችግሮች ነቅሶ በማውጣትና መንግስትና ባለድርሻ አካላት መፍትሄ እንዲፈለግላቸው ማድረግ ላይ ትኩረት አደርጎ ሊሰራ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ የአድማጭ ተመልካች የእርካታ በምን ያህል ደረጃ ላይ እንደሆነ፣ ተቀባይነቱ፤ የሚቀርቡ ፕሮግራሞች እንዲቀጥሉ እና የማይፈልጓቸው ፕሮግራሞች ደግሞ አዲስ እንዲተከሉ ለመለየት የሚያስችል፤ እንዲሁም የኮርፖሬሽኑን ቴሌቪዥንና ሬድዮንን እንዳይከታተሉ የሚያደርጋቸው ዋና ዋና ምክንያቶች፤ የስርጭቱ ጥራትና ያለበት ደረጃ ምን እንደሚመስልና ያሉትን ክፍተቶች ለመሙላት እና ለማሻሻል የሚያግዝ  የዳሰሳ ጥናት ሊያካሂድ ይገባል ፡፡
- ኮርፖሬሽኑ የአድማጭ ተመልካች ቅሬታዎችን ግብረመልስ የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት  ሊዘረጋና  ኮርፖሬሽኑ ለአድማጭ ተመልካቾች በምን ሁኔታ እና መቼ ግብረ መልስ መስጠት እንዳለበት በግልፅ የተቀመጠ የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

## አባሪ 1፡- በኦዲት ሥራ የተከለሱ ሰነዶች ዝርዝር

1. የኮርፖሬሽኑን መ/ቤቱ መቋቋሚያ አዋጅ
2. የኮርፖሬሽኑ ስትራቴጅክ እቅድ
3. የኮርፖሬሽኑ የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች፣
4. የአማረኛ ዜናና ወቅታዊ ጉዳዮች ዲቪዥን የ2015 ዓ.ም የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት፣
5. የቋንቋዎች ዜናና ወቅታዊ ጉዳዮች ዲቪዥን የ2015 ዓ.ም የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት፣
6. የኮርፖሬሽኑ የኢዲቶሪያ ፖሊሲ
7. የኮርፖሬሽኑ የቦርድና የማንጅመንት ቃለ ጉባኤ
8. የኮርፖሬሽኑ የዜናና ፕሮግራም ፎርማት የአሰራር መመሪያ
9. የኮርፖሬሽኑ የመዋቅር ሰነድ
10. የኮርፖሬሽኑ የአሳይመንት ክፍል ሪፖርቶች
11. የውስጥ ኦዲት ሪፖርቶች
12. የምስልና ድምፅ መቆጣጠሪያ መመሪያ
13. የጥቆማ ዜናዎች ለኢዲቶሪያል ኮሚቴ የቀረበው
14. የአድማጭ ተመልካች አስተያየት ሪፖርት
15. የይዘት ጥናት ሪፖርት
16. የ2009ዓ.ም የዳሰሳ ጥናት
17. የ2013 ዓ፣ም የሬድዮ ስርጭትና ተደረሽነት በተመለከተ የተጠና የጥናት ሰነድ
18. የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን መግለጫዎች
19. የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ መግለጫዎች
20. የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ ፓርቲ መግለጫዎች
21. የእናት ፓርቲ መግለጫዎች
22. የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ፓርቲ መግለጫዎች
23. የነፃነትና እኩልነት ፓርቲ መግለጫዎች
24. ለመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት መግለጫዎች
25. በኮርፖሬሽኑ ለተለያዩ የስራ ክፍሎች ቃለ መጠይቅ በማቅረብ

## አባሪ 2፡- የመመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria)

| ተ.ቁ | የኦዲቱ የትኩረት ቅጣጫዎች (Audit Issues) | የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) |
|---|---|---|
| 1 | ቦርዱ የኮርፖሬሽኑን በብቃት ለመምራት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣ | 1. የኮርፖሬሽኑ ቦርድ የራሱ የሆነ የአሰራር መመሪያ ሊያወጣ ይገባል ፡፡ |
| | | 2. ቦርዱ የመገናኛ ብዙሃንን በሚመለከት የመንግስት ፖሊሲዎችን እና ህጎችን በኮርፖሬሽኑ ተግባራዊ መሆናቸውን የሚያረጋግጥበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | | 3. ቦርዱ በኮርፖሬሽኑ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ሚዲያሞች የሃሳብና የይዘት ብዝሃነት ያላቸው ፕሮግራሞች ተቀርፀው ለህዝብ መቅረባቸውን የሚከታትለበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | | 4. ቦርዱ ኮርፖሬሽኑ በሚሰጠው አገልግሎት ህዝቡ ተጠቃሚ መሆኑን የሚገመግምበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | | 5. ቦርዱ የተለያየ አመለካከት ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶችና የህብረተሰብ ክፍሎች ሚዛናዊ የሆነ የራዲዮና የቴሌቪዥን ፍትሃዊ አገልግሎት ማግኘታቸውን የሚከታተልበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| | | |
| | | 6. ቦርዱ በራዲዮ፣ በቴሌቪዥን ፣ በዲጅታል ሚዲያ እና በሌሎች ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች የሚተላለፈውን የፕሮግራም ይዘት የሚገመግምበትና ስለሚሻሻልበት ሁኔታ ሃሳብ የሚያቀርብበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | | 7. ቦርዱ ከአድማጭ ተመልካቾች በኮርፖሬሽኑ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የሚመረምርበትና ተገቢውን ውሳኔ የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | | 8. ቦርዱ የኮርፖሬሽኑን ፕሮግራሞች በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ተደራሽ መሆናቸውን የሚከታተልበት አሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | | 9. የኮርፖሬሽኑ ቦርድ አመራር ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ሊሰበሰብ ይገባል ፡፡ |
| 2. | ??? ??? ????? ????? ? ??? ????? ? ?? ??? ? ? ??? ?? ???? ?? ????? ???? ? ??? ? ?? ?? | 10. ኮርፖሬሽኑ የአርካይቭ ፖሊሲና የአፈፃፀም ማንዋል ሊኖረው ይገባል |
| | | 11. ኮርፖሬሽኑ የኢዲቶሪያል ኮንፈረስ ማንዋል ሊኖረው ይገባል ፡፡ |
| | | 12. ኮርፖሬሽኑ የሚዲያውን ኢንዱስትሪ እና የአገሪቱን የእድገት ሽግግር ከግምት ውስጥ በማስገባት የኢዲቶሪያል ፖሊሲው በየአምስት አመቱ ሊከለስ ይገባል ፡፡ |
| | | 13. ኮርፖሬሽኑ ከተለያዩ አካላት የዘገባ ሽፋን እንዲሰጥላቸው ለሚጠይቁ አካላት የዜና መምረጫ መመሪያ ሊያዘጋጅ ይገባል፡ |

| | | |
|---|---|---|
| 3 | ??? ??? ????? ????? ? ??? ??? ?? ? ???? ??????? ?? ???? ????? ? ? ?? ?? | 14. ኮርፖሬሽኑ ኤዲቶሪያል ነፃነት በተጠበቀ እና በሥራውም ሆነ በአስተዳደሩ መንግሥትና የመንግሥት ተቋማትን ጨምሮ ከማንኛውም አካል ነፃና ገለልተኛ ሊሆን ይገባል |
| | | 15. ኮርፖሬሽኑ በቋንቋዎች ከሚያሰራጫቸው ስርጭቶች እስከ 70% ሽፋናቸው በክልሎች በሚከናወኑ ሀገራዊ ፋይዳ ያ<br>ላቸው የተሞክሮ ልውውጥ ሊደረግባቸው በሚገቡ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አደርጎ ሊሰራ ይገባል ፡፡ |
| | | 16. ኮርፖሬሽኑ መስማት የተሳናቸው ዜጎችን ተደራሽ ለማድረግ የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል ። |
| | | 17.ኮርፖሬሽኑ በአገሪቱ ሕገ መንግሥትና የምርጫ ሕግ መሠረት የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ወይም ድርጅቶችን በፍትሃዊነት የሚያገለገልበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል ፡፡ |
| | | 18. ኮርፖሬሽኑ በሚያቀርባቸው ዜናዎችም ሆነ ፕሮግራሞች የሰብአዊ መብቶች መከበራቸውን አጉልቶ የሚያሳይ የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል ፡፡ |
| | | 19. ኮርፖሬሽኑ የስርዓተ ፆታና ልዩ ድጋፍ የሚሹ ዜጎችን በተመለከተ ትኩረት አድርጎ የዘገባ ሽፋን የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | | 20. ኮርፖሬሽኑ ተቃራኒ ሃሳቦች የሚስተናገዱበትና ሃሳባቸውን የሚገልፁበት የክርክር ፕሮግራም የሚኖርበትን የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | | 21. ኮርፖሬሽኑ በሚያስተላልፋቸው የዜና ዘገባዎች |

| | | |
|---|---|---|
| | | የስርጭት ጥራታቸው በጠበቀ መልኩ ተደራሽነት ሊኖረው ይገባል ፡፡ |
| | | 22. ኮርፖሬሽኑ በሚሰራቸው የዘገባ ዜናዎች እቅድ የክልሎችን የዘገባ ስብጥር በሚያሳይ መልኩ ሊሆን ይገባል ፡፡ |
| | | 23. ኮርፖሬሽኑ የሚሰራቸው የዜናዎችና ፕሮግራሞች የዘገባ ይዘትና የስብጥር ብዛት በሚያሳይ መልኩ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | | 24. ኮርፖሬሽኑ በሚሰራቸው የዜና ዘገባ እቅድ የሁነትና የፕሮጅክት የዜና ብዛት በሚያሳይ መልኩ ሊቀመጥ ይገባል፡፡ |
| 4 | ??? ??? ??? ????? ? ??? ? ? ?? ??? ???? ? ???? ???? ? ???? ? ??? ? ?? ?? | 25. ኮርፖሬሽኑ በሚያቀርባቸው ዘገባዎች እና ፕሮግራሞች ላይ የህዝቡን ስሜት ለማወቅ በናሙና ላይ የተመሰረተ የዳሰሳ ጥናት ሊያከናውን ይገባል ፡፡ |
| | | 26. ኮርፖሬሽኑ ገለልተኛና ሙያዊ ብቃት ባላቸው የውጭ አካላት የአድማጭ ተመልካች ጥናት ሊያካሂድ ይገባል፡፡ |
| | | 27. ኮርፖሬሽኑ የአድማጭ ተመልካች ግብረመልስ የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | | 28. ኮርፖሬሽኑ የአድማጭ ተመልካች ቅሬታዎች የሚያስተናግድበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |

## አባሪ 3፡- በኢትዮጵያ ሬዲዮ እና በኤፍ ኤም 97.1 ከአድማጭ ተመልካች ግበረ መልስ ሪፖርት ውስጥ ከማህበረሰቡ ከቀረቡ ቅሬታዎች ውስጥ ለማሳያ ያህል

- ጥር 2013 ዓ.ም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ሬድዮ እና በኤፍ ኤም 97.1 ላይ ስርጭትን አስመልክቶ 40 አስተያየቶች የተሰጡ ሲሆን ከአድማጭ ተመልካቾች በተገኘው መረጃ መሠረት ችግሮቹን በሥርጭት መቆራረጥና ጨርሶ መቋረጥ፤ በጥራት መጓደልና ባለመሰማት፤ በስርጭት ተደራሽ ባለመሆን ቅሬታቸውን ያቀረቡ መሆኑ፡፡
- በነሀሴ ወር 2013 ዓ.ም. ለኢትዮጵያ ሬዲዮ እና በኤፍ ኤም 97.1 ከተሰጡት 533 አስተያየቶች በስርጭት መቋረጥ 40 (7.5%)፣ መቆራረጥ 26 (4.6%) እና የድምጽ ጥራት መጓደልና ወጣ ገባ ያገጠማቸው 7(1.13%) በድምሩ 73 (13.71%) የስርጭት ችግር የታየባቸው መሆኑ፡፡
- በጥቅምት ወር 2014 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ሬድዮ እና በኤፍ ኤም 97.1 ላይ ስርጭትን አስመልክቶ 10 ወይም ከአጠቃላይ የሬዲዮ አስተያየቶች ብዛት 1.86% የተሰጡ ሲሆን ከአድማጭ ተመልካቾች አስተያየት በተገኘው መረጃ መሠረት በስርጭት ተደራሽነት፣ በሥርጭት መቋረጥ፣ መቆራረጥ እና የጥራት መጓደልና ወጣ ገባና የማለት ሁኔታ የነበር መሆኑ፡፡
- በታህሣሥ ወር 2014 ዓ.ም. ለኢትዮጵያ ሬድዮ እና በኤፍ ኤም 97.1 ላይ ስርጭትን አስመልክቶ 44 ወይም ከአጠቃላይ የሬዲዮ አስተያየቶች ብዛት 9 ነጥብ 11 ከመቶ የያዘ ሲሆን ካለፈው ህዳር/2014 ጋር ሲነጻጸር ደግሞ በ30 ብልጫን አሳይቷል፡፡
- በግንቦት ወር 2015 ዓ.ም በኢትዮጵያ ሬዲዮ ላይ ስርጭትን አስመልክቶ 35 ወይም ከአጠቃላይ የሬዲዮ አስተያየቶች ብዛት 17.50% የያዘ ሲሆን ከአድማጭ ተመልካቾች አስተያየት በተገኘው መረጃ መሠረት በስርጭት ሙሉ በሙሉ መቋረጥ፣መቆራረጥና በጥራት አለመደመጥ እንዳለ ተለይተዋል፡፡*በአማራ፣በኦሮሚ፣ደቡብ፣ደቡብ ምዕራብ፣አፋር* *እና ሶማሌ* ክልሎች በተደጋጋሚ የስርጭት ችግሮች የተነሱባቸው መሆኑ ፡፡
- በየካቲት ወር 2015 ዓ.ም.በኢትዮጵያ ሬዲዮ ላይ ስርጭትን አስመልክቶ 54ወይም ከአጠቃላይ የሬዲዮ አስተያየቶች ብዛት 22.50% የያዘ ሲሆን ከአድማጭ ተመልካቾች አስተያየት በተገኘው መረጃ መሠረት በስርጭት ሙሉ በሙሉ መቋረጥ፣መቆራረጥና በጥራት አለመደመጥ እንዳለ ተለይተዋል፡፡*በአማራ፣በኦሮሚ፣ደቡብ፣ሲዳማ፣ቤኒሻንጉል* *እና ትግራይ* ክልሎች በተደጋጋሚ የስርጭት ችግሮች የተነሱባቸው መሆኑ ፡

**አበሪ 4 ፦** በኮርፖሬሽኑ በ2015 ዓ.ም የተሰሩት የዜና ስብጥሮች የሚያሳይ

ኮርፖሬሽኑ በቋንቋዎች ከሚያሰራጫቸው ስርጭቶች በማእከልና በክልሎች በ2015ዓ.ም የተሰሩት ዜናዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል ፡፡

| ተቁ | ክልል/አስተዳደር | የዜናዎች ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | ፌደራል | 13552 |
| 2 | ኦሮሚያ | 6622 |
| 3 | አፋር | 858 |
| 4 | ድሬዳዋ | 418 |
| 5 | አዲስ አበባ | 3036 |
| 6 | ሶማሌ | 352 |
| 7 | ትግራይ | 1045 |
| 8 | አማራ | 737 |
| 9 | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | 407 |
| 10 | ጋምቤላ | 363 |
| 11 | ሃረሪ | 275 |
| 12 | ደቡብ | 660 |
| 13 | ሲዳማ | 559 |
| 14 | ደቡብ ምእራብ | 253 |
| 15 | የዉጭ | 2411 |
| **ጠቅላላ ድምር** | | **31548** |

# አባሪ 5፡- የራዲዮ የስርጭት ጥራትና ተደራሽነትን ችግር ያለባቸው አካባቢዎች የሚያሳይ መረጃዎች

## ፍቼ ማሰራጫ ጣቢያ

### ደካማ የስርጭት ቦታዎች

- ኤፍኤም 89.6 ሥርጭት በጫንጮ፤ደብረወርቅ ፤ብቸና መሃል ከተማ ደካማ መሆኑ
- ወረጃርሶ፡አለልቱ፡አብቹ፡ቅምብብት፡ውጫሌ፤ግራርጃርሶ፡ደብረሊባኖስ፡ያያ ጉለሌ፡ጅዳ እና ኪዮ ወረዳዎች የኢትዮጵያ ሬዲዮ ስርጭት ቢኖርም ወደ ገጠር ቀበሌዎች ጥራቱ ደካማ መሆኑ

### የማይሸፈኑ የስርጭት ቦታዎች

- ሱሉልታ ግንደወይን ና ጉርፍኤፍኤም 89.6 ሥርጭት የማይደርስባቸው ቦታዎች ናቸው፡፡
- የመርጦ ለማርያም ከተማ የኢትዮጵያ ሬዲዮሥርጭት በመካከለኛ ሞገድም ሆነ በኤፍ ኤም ስርጭት የሌለው መሆኑ
- ደራ፡ኢዳቡ አቦቴናደገም ወረዳዎች ደግሞ የኢትዮጵያ ሬዲዮ ሥርጭት የማይደርስባቸው መሆኑ ፡፡

## ደብረ ማርቆስ ማሰራጫ ጣቢያ

### ደካማ የስርጭት ቦታዎች

- የኤፍኤም93.1 ሥርጭት ደካማ የሆነባቸው አካባቢዎች ሉማሜ፣አማኑኤል፣ማንኩሣ፣ቡሬ፣ፈንድቃ፤አዴት መስገድና አዲስ አበባ መውጫ፣ቅንባብ፣አስተሪዬ፣ደብረወርቅ መሐል ወደ አዲስአበባ መውጫ ላይ ሥርጭቱ በጣም ደካማ መሆኑ
- ቻግኒ መውጫ፣አዲስአበባ መውጫና ማረሚያ ቤት አካባቢ ኤፍኤም 93.1 ሬዲዮሥርጭት ደካማ መሆኑ
- የእንጅባራ ከተማ የሬዲ ዮሥርጭት በጣም ደካማ መሆኑ
- የዳንግላ ከተማ፤ከባህርዳር ዳንግላ መግቢያ ቀበሌ 04 አደባባይ፣አየርጤና ቀበሌ አንድ እና ጃዊ መውጫ በተደረገው ልኬት የሬዲዮሥርጭቱ በጣም ደካማ መሆኑ

- አዊ ብሄረሰብ ዞን አስተዳደር የሬዲዮ ስርጭት በአብዛኛዉ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ከፍተኛ የጥራት ችግር ያለባቸውመሆኑ ፡፡ እንዲሁም አንዳንድ ወረዳዎችና የገጠር ቀበሌዎች ደግሞ የኢትዮጵያሬዲዮ ሥርጭት  የማይደርስ መሆኑ

**የማይሸፈኑ የስርጭት  ቦታዎች**

- በዳንግላ፡አዲስቅዳም፤ቲሊሊ፤ግምጃቤት፣መሽንት መግቢያ መሃልና መውጫ፤መራዊ፣አምቦመስክ፣ሞጣከተማ፤ከባርህርዳርመግቢያ፣መሃልከተማ፣አደባባይና ሞጣ አዲስ አበባ መዉጫ የሬዲዮሥርጭት የሌለ መሆኑ፡
- ከባህርዳር ከተማ ወደ ዳንግላ መውጫ ይነሳ አካባብ፤ቀራንዮ፣ግንደወይን፣ፈለጌ ብርሃን፤አዲስቅዳም እና መርጦለማርያም ኤፍኤም 93.1 ሬዲዮ ሥርጭት የማይደርስባቸው አካባቢዎች መሆናቸው

## <u>3. ባህር ዳር ማሰራጫ ጣቢያ</u>

**ደካማ የስርጭት ቦታዎች**

- ኤፍኤም 94.5 ጢስ አባይ መገንጠያ ነግዳማርያም፤እንቁርጥ ወደጐንደርመውጫ ዘንዘላማን አልፎሥርጭቱ በጣም ደካማ መሆኑ ፡
- ባህርዳር ከተማ ግሽአባይ፤ጣና፤ፋሲሎ፤ዳግማዊ ምኒሊክ፤አፄቴዎድሮስ እና በላይዘለቀ ክፍለ ከተሞች ኤፍኤም 94.5 የሬዲዮ ስርጭት በተወሰነ ደረጃ የሚሰራ መሆኑ
- ከምዕራብ ጎጀም ዞን ሬዲዮ  ስርጭት እየሰራ የድምፅ ጥራት ችግር ያለባቸዉ ወረዳዎች እና ከተማ አስተደደሮች ይልማናዴንሳ፤ሰሜንአቸፈር፡ሰሜንሜጫ፤ቡሬዙሪያ፤ደቡብአቸፈር፤ቡሬከተማ እና ጎንጃ ቆላላ ወረዳዎ ናቸው

**የማይሸፈኑ የስርጭት  ቦታዎች**

- ከባህርዳር በዳንግላ መውጫ አካባቢ፤መሸንቲ መግቢያ እና ከአራቱም አቅጣጫዎች ከባህርዳር ከተማ ወጣ እንዳለ የኤፍኤም 94.5 ሬዲዮሥርጭትየማይደርስመሆኑን
- ኢትዮጵያ ሬዲዮ ኤፍኤም 94.5 እና ኤፍኤም 93.1 ሬዲዮ ስርጭት ጭራሽ የማይደረስባቸዉ ወረዳዎች እና ከተማ አስተዳደሮች ደግሞ

ደቡብሜጫ፤ደጋዳሞት፤ወንበርማ፤ፍኖተሰላምከተማ፤ቋሪት፤ጃቢጣህናን፤ሰከላ እና ደምበጫ ዙሪያ መሆናቸው

## 4. ጐንደር ማሰራጫ ጣቢያ

### ደካማ የስርጭት ቦታዎች

- ደቡብ ጎንደር ዞን ካለዉ 15 /አስራአምስት /ወረዳዎችዉስጥ በ10 /አስሩ/ ፍርጣ፤ድብረታቦር፤ላይጋይንት፤ታችጋይንት፤ስማዳ፤እንዳቤት፤ፎገራ፤ወረታ፤ሊቦከምከም እናጉና ወረዳዎች ኢትዮጵያ ሬዲዮ ስርጭት ጥራት ደካማ መሆኑ

### የማይሸፈኑ የስርጭት ቦታዎች

- በጐንደር ማሰራጫ ጣቢያ የማይሸፈኑ አካባቢዎች ወረታ፣አዲስዘመን፣አርንኖ፣አጠጥበር፣ወረታማገንጠየ፣አይምባ፤ጭልጋነበሩ፣ወጅ፣አመድበርእ ና አለምሳጋ አካባቢዎች ናቸው፡፡
- በደብረታቦር ከተማመግቢያ፣መሐልና ወልድያ መውጫ ላይ የኢትዮጵያሬዲዮ ሥርጭት እንደሌለ በእጅሬደዮ፣በሞባይልና በፊልድ እስትሬንግዝ ልኬት የተረጋገጠ መሆኑ
- ከማዕከላዊ ጐንደር ዞን ካለው 17 ወረዳዎች መካከል በ13/አሰራሳሶት/ ወረዳዎች ማለትምአለፋ፣ጠቁግ፣ምስራቅደምቢያ፣ምዕራብ ደምቢያ፤አዲሲጭልጋ/ቁጥር 1/፣ነበሩ ጭልጋ /ቁጥር2/ ፤ወገራ፤ታችአርማጨሆ፤መሃልአርማጨሆ፣እንፍራንዝ፤ላይአርማጨሆ፤አይከል ከተማና አምባጊዮርጊስ ወረዳዎች የኢትዮጵያ ሬዲዮ መካከለኛ ሞገድ ሥርጭት የማይደረስባቸው መሆኑ
- በማዕከላዊ ጐንደር ዞን በ17ቱም ወረዳዎች የደባርቁ ኤፍኤም 88.7 ሬዲዮሥርጭት የማይደርስ መሆኑ
- የአብናት፤አዲስ ዘመን፤ደራ፤እስቴ እና መካነ እየሱስ ደግሞ የኢትዮጵያሬዲዮ ስርጭት የማይሰራባቸዉ ወረዳዎች መሆናቸው ፡፡
- አብናት ወረዳ ብቻ የደባርቅኤፍኤም 88.7 ስርጭት የሚደርስ ሲሆን ዞኑ ያለዉ ሌሎች ወረዳዎች ዉስጥ ኤፍኤም 88.7 ስርጭት የሌለ መሆኑ ፤፡

## ደባርቅ ማሰራጫ ጣቢያ

### ደካማ የስርጭት ቦታዎች

- ደባት፣ደባርቅ ከተማ መሃል፡- መውጫ፤በበየዳ፤በአደአረቃይ፤በጃናአሞራ፤በደባርቅና በዳባት ወረዳዎች የኢትዮጵያ ሬዲዮ ስርጭት በመካከለኛ ሞገድ ቢኖርም ጥራት የሌለውና የመቆራረጥና እሽታ ያለው መሆኑ

**የማይሸፈኑ የስርጭት ቦታዎች**

- በጠለሚት ወረዳ ፡በዳባት ወረዳ የኤፍኤም 88.7 ሙሉ በሙሉ የማይሰራ መሆኑ ፡

**<u>በቆሪ ማሰራጫዎች</u>**

**በደካማ የሚደመጥባቸው**

- በኤፍ-ኤም 93.1 ቤሂራዊ ሬድዮ አዳማ ፤ አርሲ ደካማ መሆኑ

**የማይሸፈኑ የስርጭት ቦታዎች**

- ኢትዮጵያ ሬዲዮ የማይደመጥባቸው አራት አካባቢዎች ማለትም አዳማ ፤ አርሲ አሰላ ፤ ኢተያ እና ወንጂ ከተሞች ናቸው፡፡
- አርሲ አሰላ ላይ የአዲስ አበባው 873 khz መካከለኛ ሞገድ ስርጭት የማይደመጥ መሆኑ ፡፡ እንዲሁም የአካባቢው ነዋሪዎች የጣቢያውን ስርጭት በኤፍ ኤም እና መካከለኛ ሞገድ የማያገኙ መሆኑ ፡፡

**<u>ከአዳማ እስከ ድሬደዋ</u>**

**ደካማ የስርጭት ቦታዎች**

- **የኢትዮጵያ ሬድዮ በ873 ወይንም 855** በደካማ ስርጭት የሚደመጥባቸው ከተሞች፡- ቆቦ፣ መልካጀብዱ፣ቁልቢ፣ጨለንቆና ሀረማያ መሆናቸው

**የማይሸፈኑ የስርጭት ቦታዎች**

- የኢትዮጵያ ሬዲዮ መካከለኛ ሞገድ በ873 እና 855 khz በጭራሽ የማይደመጥባቸው ከተሞች ተከታዮቹ ወለንጪቲ፤ መተሀራ ፤ አዋሽ 7 ፤ ሂርና ፤ መኤሶ ፤ ደባሶ ፤ አሰበ ተፈሪ ( ጭሮ ) ፤ ቦረዳ ፤ ካራ ሚሌ ናቸው
- **ኢትዮጵያ ሬድዮ በ873 ወይንም 855 ሞገድ** ምንም አይነት ስርጭት የማይደርስባቸው አካባቢዎች፡- ወለንጪቲ፣ መተሃራ፣ አዋሽ-7 ሂርና፣ሚኤሶ፣ ደባሶ፣ አሰበተፈሪ፣ ቦረዳ፣ ካራሚሌ ናቸው ፡፡

## <u>ከሀረር እስከ ጅግ ጅጋ</u>

**ደካማ የስርጭት ቦታዎች**

በመካከለኛ ሞገድ 855 khz የኢትዮጵያ ሬዲዮ ስርጭት ከተሞች ቀብሪ በያህ እና ደገ ሀቡር ደካማ መሆኑ

**የማይሸፈኑ የስርጭት ቦታዎች**

- የኢትዮጵያ ሬዲዮ መካከለኛ ሞገድ ስርጭቱ በምንም መንገድ የማይደመጥበት ከተማ ደግሞ ቀብሪ ደሀር መሆኑ

## <u>ከቀብሪ ደሀር እስከ ጉዴ</u>

**ደካማ የስርጭት ቦታዎች**

- **ጉዴ መካከለኛ ሞገድ** 1260 የማይደርሳቸው አካባቢዎች፦ ቀብደሃር፣ካፕቲክ፣ላሴንገር፣ዳናን ናቸው፡፡

## <u>ሻሸመኔ ማሰራጫ ጣቢያ</u>

**ደካማ የስርጭት ቦታዎች**

- የሻሸመኔ የኤፍኤም ማሰራጫ ጣቢያ ሞሮቾ፣ ይርጋ አለምና አዲሎ ዝዋይ፣ አዳሚ ቱሉ፣ ሾኔ እና አላባ ቁሊቶላይ ደካማ የስርጭት ሽፋን የሆነባቸው ቦታዎች መሆናቸው ፡፡

## ሀገረ ሰላም ማሰራጫ ጣቢያ

**ደካማ የስርጭት ቦታዎች**

- የሀገረ ሰላም የኤፍኤም ማሰራጫ ጣቢያ ወናጎና ቦሬዲላ፣ ይርጋ ጨፌ፣ ሶዶና አርባ ምንጭ ላይ ደካማ የስርጭት ሽፋን የሆነባቸው ቦታዎች ናቸው፡፡

## <u>ክብረ መንግስት ማሰራጫ ጣቢያ</u>

**ደካማ የስርጭት ቦታዎች**

- የክብረ መንግስት የኤፍኤም ማሰራጫ ጣቢያ የሻኪሶን ጥቂት የከተማዋን ከፍታ ቦታዎች በደካማ ሲግናል የሚሸፍን መሆኑ

## <u>ነገሌ ቦረና 1485 KHZ</u>

**ደካማ የስርጭት ቦታዎች**

- የነገሌ መካከለኛ ሞገድ ማሰራጫ ጣቢያ የዋዴራ ከተማንና ዙሪያዋን በደካማ ሲግናል የሚሸፍን መሆኑ

**የማይሸፈኑ የስርጭት ቦታዎች**

- የነገሌ መካከለኛ ሞገድ ማሰራጫ ጣቢያ ከተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ አሁን ላይ አነስተኛ የፓወር አቅም ያለው ከመሆኑ አንፃር ከዋዴራ ከተማን ውጪ የመሸፈን አቅም የሌለው መሆኑ ፡፡

<u>ሶዶ 97.1 MHZ</u>

**ደካማ የስርጭት ቦታዎች**

- የሶዶ የኤፍኤም ማሰራጫ ጣቢያ የምዕራብ አባይና ብርብር ከተሞችን በደካማ ሲግናል የሚሸፍን መሆኑ
- **አርባ ምንጭ** 828 KHz

**የማይሸፈኑ የስርጭት ቦታዎች፡**

- በ 50 ኪ.ሜ (ምእራብ አባያ) እናበ 30 ኪ.ሜ (ብርብር) ላይ ስርጭቱ የማይደርስ መሆኑ

<u>ሮቤ 972 KHZ</u>

**ደካማ የስርጭት ቦታዎች**

- በ30ከ. ሜ (አዳባ ዲንሾ) ላይ ደካማ መሆኑ


## አባሪ 6፡- ኢዜማ ካወጣቸው መግለጫዎች በኮርፖሬሽኑ የዘገባ ሽፋን የሰጣቸውና ያልሰጣቸው መግለጫዎች የሚያሳይ

- ኢዜማ ካወጣቸው መግለጫዎች  ውስጥ  ኮርፖሬሽኑ  የዘገባ ሽፋን ከሰጣቸው ውሰጥ  የሚከተሉት ናቸው
  - ፓርቲዎች የዴሞክራሲ ልምምድን ከራሳቸው እንዲጀምሩ ኢዜማ መጠየቁ
  - ከሰሜኑ ጦርነት ጋር በተያያዘ የውጪ ሀገራት ጫና
  - ብሔራዊ ምክክሩ የአገርና የሕዝብ ፕሮጀክት ነው
  - ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ የምርጫውን መካሄድ የሚጠይቅ ነው
  - መንግሥት ልዩነቶችን በማጥበብ፣ በመቀራረብና በመመካር ሀገር የመምራት ኃላፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣ ኢዜማ አሳሰበ
  - ያለምንም የፖለቲካ ልዩነት ለኢትዮጵያ ህልውና በጋራ መቆም አለብን
  - የውጭ ጫናን ለመቋቋም የውስጥ ትብብርና አንድነታችን መጠናከር አለበት
- ኢዜማ ካወጣቸው መግለጫዎች  ኮርፖሬሽኑ የዘጋባ ሽፋን ካልሰጣቸው  ውሰጥ የሚከተሉት ናቸው
  - የጥላቻ ፖለቲካን የፈለፈለው የብሔር አስተሳሰብ ሃይማኖት ውስጥም ገብቶ ሌላ ትርምስ ሲፈጥር ዝም ሊባል አይገባም  ብሎ የተሰጠ መግለጫ
  - መንግስት ከታረዙት ዜጎች ጉሮሮ የሚነጥቀው ሰብአዊ እርዳታ ሃገራችን ያለችበትን የከፋ የሌብነት ሙስና እና ኢ ሰብአዊነት ደረጃ የሚያሳይ ነው ብሎ የተሰጠ መግለጫ
  - በትላንትናው እለት በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል መተከል ዞን በዜጎች ላይ የተፈፀመውን ጥቃት አስመልክቶ ከኢትዮጲያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ የተሰጠ መገለጫ
  - ገዢው ፓርቲ ብልፅግና መንግስትን እና ፓርቲን በደበላለቀ መልኩ በመንቀሳቀስ የዜጎችን ሃብት  ለፓርቲ ጥቅም እያዋለ


መሆኑን ተከትሎ ከኢትዮጲያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ ኢዜማ የተሰጠ መግለጫ

- በአማራ ክልል ስለተከሰተው አለመረጋጋትና የአስቸኮይ ጊዜ አዋጁን አስመለክቶ በዛሬው ዕለት ነሐሴ 02/2015 ዓም ከኢትዮጲያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትሕ የተሰጠ መግለጫ
- የሰለም ዕጦቱና አለመረጋጋቱ ምንጩ በጠራ የፖለቲካ መስመር ላይ መቆም ያልቻለው አቆምም ሆነ አቅም የሌለው የብልፅግና አመራር ነው የተሰጠ መግለጫ
- በኢዲስአበባ ት/ቤቶች ላይ የኦሮሚያ ክልል ሰንደቅ ዓላማ መሰቀልን ተከትሎ ኢዜማ ሕዳር 29/2015 ዓ.ም ያወጣው መግለጫ
- የኢትዮጲያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በምስራቅ ወለጋ ወረዳ ንፁህን ዜጎች ላይ የደረሰውን አሰቃቂ ጭፍጨፋ አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ
- የኢትዮጲያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በአዲስ አበባ ከተማ የመሬት አጠቃቀም እና የጋራ መኖሪያ ቤቶች ማስተላለፍ ጋር ተያይዞ ያሉ ችግሮች ላይ ያደረገውን ምርመራ ውጤት ይፋ የሚያደርግበት ጋዜጣዊ መግለጫ
- የኢትዮጲያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ(ኢዜማ) ገዢው ፓርቲ ያለበቂ ውይይት እና ግልፅነት በጎደለው መልኩ የኢትዮ ቴሌኮምን ከፊል ድርሻ ለመሸጥ እየሄደበት ያለው ጥድፊያ በአስቸኮይ እንዲቆም የጠየቀበትን ጋዜጣዊ መግለጫ
- የደቡብ ክልል ውስጥ የሚገኙ የዞኑ አስተዳደሮች ያቀረቡትን ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ አስመልክቶ መንግስት አስጠናሁ ያለው የክላስተር አከላለል አስመልክቶ ከኢትዮጲያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የተሰጠ መግለጫ
- የዜጎች ሰብአዊ መብት መከበር በምንም ምክንያት እና በማንኛውም ጊዜ ለድርድር የማይቀርብ ነው የሚሉት ናቸው፡፡

## አባሪ 7 ፡-የኮርፖሬሽኑ ድርጅታዊ መዋቅር




## የዜናና ወቅታዊ ዘርፍ መዋቅር




## አበሪ 8፡- የአሰራር ስርዓት መግለጫ (System Description)


በከፍተኛ አመራሮች  የሚመራ የኢቢሲ ኢዲቶሪያል ኮንፈረስ አደረጃጀትና ውሳኔ መስጠት ሂደት ላይ የሚሳተፍ ክፍሎች የሚያሳይ




## የሁነት  የዜና የስራ ፍሰት





## ፕሮጅክት የዜና የስራ ፍሰት




የአሳይመንት ዴስክ የሁነት ዜናዎችን ጭምር በማየት የመስሪያ ግብዓትና ተጨማሪ አቅጣጫ ካለ ለዋናው ኤዲቶሪያል አቅርቦ እንዲፀድቁ ያደርጋል
ለስራው ለተመደበው ሪፖርተር ካሜራ፣መኪናና የሚያስፈልግ ተጨማሪ ግብዓት ይመደባል
ስምሪት፣መረጃ እና አስፈላጊ ግብዓቶች ይሰበሰባሉ
ስክሪፕት መጻፍ፣የእርትኦት ስራ፣ከቪዲዮ ኤዲተር ጋር በመሆን የፕሮዳክሽን ስራ ተጠናቆ ይሰራል
ፕሮዳክሽኑ የተቀመጠለትን ግብና የጥራት ደረጃ ማሟላት በማረጋገጥ ዋና አዘጋ ለአየር እንዲበቃ ያደርጋል

## የአድማጭ ተመልካች  ግብረ መልስ ትንተና የሚያሳይ የስራ ፍሰት



# አባሪ 9 ፡-የሬዲዮ ትራንስሚተሮች የማስተላለፍ አቅማቸውን የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የማሰራጫ ጣቢያ ስም | የሥርጭት ሞገድ | የማሰራጪት አቅም | አሁን ያለው አቅም | ምርመራ | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| FMADDIS | | | | | | |
| 1. | መቀሌ ኤፍኤም | 97.1 Mhz | 1KW | 940 Watt | | FM ADDIS |
| 2. | መ ቱ ጎ ሬ ኤፍኤም | 97.1 Mhz | 3KW | 2700Watt | የአካባቢ.ቁንቁበኢ.ንሰርሽንያሰራጫል ፡፡ | |
| 3. | ሻሸመኔ ኤፍኤም | 97.1 Mhz | 3KW | 3000 Watt | | |
| 4. | ባሌጎባ ኤፍኤም | 97.1 Mhz | 1KW | 945Watt | | |
| 5. | አሳኢ.ታ ኤፌኤም | 97.1Mhz | 1Kw | 752Watt | | |
| 6. | አርባምንጭ ኤፍኤም | 97.1 Mhz | 1KW | 910Watt | | |
| 7. | አክሱም ኤፍኤም | 102.1 Mhz | 3KW | 1000 Watt | | |
| 8. | አዳማ ኤፍኤም | 97.1Mhz | 1KW | 900Watt | | |
| 9. | አዶሎወዩ (ክ/መንግስት) ኤፍኤም | 97.1 Mhz | 1KW | 730Watt | | |
| 10. | ወላይታሶዶ ኤፍኤም | 97.1 Mhz | 1KW | 890Watt | | |
| 11. | ደሴ ኤፍኤም | 97.1Mhz | 1KW | 836 Watt | | |
| 12. | ድሬዳዋ ኤፍኤም | 97.1 Mhz | 1KW | 890Watt | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 13. | ጅጅጋ ኤፍኤም | 93.1 Mhz | 3KW | 2850 Watt | የአካባቢ ቁንቁበኢንሰርሽንያሰራጫል ፡፡ | |
| 14. | ጋምቤላ ኤፍኤም | 97.1 Mhz | 1KW | 700 Watt | | |
| 15. | ፋሪኤፍ ኤምአዲስ | 97.1Mhz | 3kw | 3000kw | | |
| FMNATIONAL RADIO | | | | | | |
| 1. | ሀገረሰላም ኤፍኤም | 104.7Mhz | 3KW | 2786Watt | | FM NATIONAL RADIO |
| 2. | ሁመራ ኤፍኤም | 93.1Mhz | 3KW | 1500 Watt | | |
| 3. | ቢላ ኤፍኤም | 93.1 Mhz | 3KW | 1000watt | በፀጥታ ምክንያት ስርጭት አቋሟል | |
| 4. | ባ/ዳር ኤፍኤም | 104.7Mhz | 1KW | 758Watt | የአካባቢ ቁንቁበኢንሰርሽንያሰራጫል ፡፡ | |
| 5. | ቦንጋ ኤፍኤም | 93.1 Mhz | 3KW | 2850Watt | | |
| 6. | ተንዳሆ ኤፍኤም | 93.1 Mhz | 3KW | 1950 Watt | | |
| 7. | ነቀምት ኤፍኤም | 93.1 Mhz | 1KW | 210Watt | | |
| 8. | አምቦኤ ፍኤም | 97.1 Mhz | 1KW | 724Watt | ኤፍኤምአዲስበኢንሰርሽንያሰራጫል ፡፡ | |
| 9. | አሶሳ ኤፍኤም | 93.1Mhz | 3KW | 2888Watt | | |
| 10. | አዲረመፅ | 101.2 Mhz | 3KW | 1650Watt | | |
| 11. | ደ/ብርሀን(አንኮበር) ኤፍኤም | 93.1 Mhz | 1KW | 780Watt | | |
| 12. | ደባርቅ ኤፍኤም | 93.1 Mhz | 3kW | 2800Watt | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 13. | ጅማ ኤፍኤም | 93.1Mhz | 3KW | 1436 Watt | | |
| 14. | ግልገልበለስ ኤፍኤም | 93.1 Mhz | 1KW | 650Watt | | |
| 15. | ጎንደር ኤፍኤም | 97.1 Mhz | 3KW | 1500 W | ኤፍኤምአዲስበኢንሰርሽንያሰራጫል ፡፡ | |
| 16. | ጮቄተራራ (ደ/ማርቆስ) | 93.1 Mhz | 3KW | 3000W | በፀጥታ ምክንያት ስርጭት አቁሟል | |
| 17. | ፋራብሄራዊአገልግሎት ኤፍኤም | 93.1Mhz | 3kw | 2950Watt | | |
| 18. | ፍቼ ኤፍኤም | 104.7 Mhz | 3KW | 3000 KW | | |
| MWNATIONAL RADIO | | | | | | |
| 1. | ሀረርብሄራዊ ሬድዮ | 855khz | 100KW | 100KW | | MW NATIONAL RADIO |
| 2. | መቀሌ ብሄራዊ ሬድዮ | 1044khz | 50KW | 34KW | | |
| 3. | መቱ ብሄራዊ ሬድዮ | 684khz | 50KW | 20KW | | |
| 4. | ባሌሮቤ ብሄራዊ ሬድዮ | 972 khz | 50KW | 40KW | | |
| 5. | ነጌሌቦረናብሄራዊ ሬድዮ | 1485khz | 25KW | 24.5KW | በቴክኒክ ምክንያት ስርጭት አቁሟል | |
| 6. | አ/ምንጭ ብሄራዊ ሬድዮ | 828khz | 50KW | 38KW | | |
| 7. | ደሴ ብሄራዊ ሬድዮ | 891 khz | 50KW | 35KW | | |
| 8. | ጌጃዴራ ብሄራዊ ሬድዮ | 873khz | 50KW | 50KW | | |
| 9. | ጎዴ ብሄራዊ ሬድዮ | 1260khz | 25KW | 25KW | | |
| የውጪቋንቋዎች | | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ፉሪ የውጪ ቋንቋ ኤፍኤም | 104.7 Mhz | 3KW | 3020 Watt | | |